# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 232 ሚያዝያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## “የኢትዮጵያ በፈተናዎች ያለመበገር ፅናት በመዋቅራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎች ማሳያነት ይገለጣል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ:- የኢትዮጵያ በፈተናዎች ያለመበገር ፅናት የምጣኔ ሀብት መረጋጋትንና ምርታማነትን ባስቀደሙት በመዋቅራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎቿ ማሳያነት ይገለጣል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የልዑካን ቡድናቸው በኬንያ በተዘጋጀው የዓለም አቀፉ የልማት ማኅበር (አይዲኤ) 21ኛ የማሟያ ጉባኤ ላይ ተሳትፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግር፤ የኢትዮጵያ በፈተናዎች ሁሉ የተሻገረ ያለመበገር ፅናት የምጣኔ ሀብት መረጋጋትንና ምርታማነትን ባስቀደሙት በመዋቅራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎቿ ማሳያነት ይገለጣል ብለዋል።

« የኢትዮጵያ በፈተናዎች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ጤናማ ዜጋና ጽዱ ከተማን የመፍጠር ጥሪ

አዲሱ ገረመው




ከኢትዮጵያ ሕግጋት አብዝተው ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል “ክልክል ነው” የሚለው ማስጠንቀቂያ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ጥቅስ መነሻነት ብዙ ማስታዎቂያዎች እንዲያው ለደንቡ በሚመስል ሁኔታም ቢሆን የተከለከሉ ነገሮች ተለጥፈው ማየታችን የየዕለት ምልከታችን ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ደግሞ በየጥጋጥጉ ተለጥፎ የሚታየው “መሽናት ክልክል ነው” የሚለው ማስጠንቀቂያ ይጠቀሳል፡፡

በአዲስ አበባ የተለያዩ አውራ ጎዳናዎችን ጨምሮ “መሽናት በሕግ ያቀስጣል” የሚሉ ማስጠንቀቂያዎች ተለጥፈው ቢታዩም ክልከላው በተለጠፈባቸው ሥፍራዎች ጭምር ብዙዎች ሲጸዳዱ ማየት የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ መንገድ ላይ መጸዳዳትን እንደ ነውር

« ጤናማ ዜጋና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ተመስገን ጥሩነህ

## ረቂቅ ሠነዱ ሀገራዊ ልማትና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ያግዛል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ የኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ ረቂቅ ሠነድ መዘጋጀቱ ሀገራዊ የልማት ፕሮግራምን ለማሳደግና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ያግዛል ሲሉ ምክትል

«ረቂቅ ሠነዱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “በኮሪደር ልማቱ የተነሱ የቤተክርስቲያን ሀብቶችን መልሶ የማልማቱ ሥራ በትብብር እየተሠራ ነው”

- ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ፓትርያርክ



ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ በኮሪደር ልማት የተነሱ የቤተክርስቲያን ሀብቶች መልሶ የማልማት ሥራ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በትብብር እየተሰራ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን

« በኮሪደር ልማቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ክልሎቹ የስድስተኛ እና የስምንተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ለመስጠት ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የስድስተኛ እና የስምንተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ለመስጠት ዝግጅታቸውን እያጠናቀቁ መሆናቸውን የኦሮሚያና የሲዳማ ክልል ትምህርት ቢሮዎች አስታወቁ፡፡

የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ገላና ወልደሚካኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በክልሉ የስድስተኛ እና የስምንተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ለመስጠት ዝግጅቶች ተጠናቀዋል። ተማሪዎችም ምዝገባቸውን በኦንላይን እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡

በክልሉ ስድስተኛ ክፍል ከ700 ሺ በላይ ተማሪዎች ለመፈተን የተመዘገቡ ሲሆን፤ የስምንተኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ ደግሞ ከ600 ሺ በላይ ተማሪዎች መመዝገባቸው ገልጸዋል፡፡ የፈተና ወረቀት ህትመትን በተመለከተ የስድስተኛ ክፍል ፈተና ህትመት ተጠናቆ መጋዘን የገባ ሲሆን፤ በተመሳሳይ የስምንተኛ ክፍል ፈተና የመጀመሪያው ህትመት መጠናቀቁን ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም ግንቦት 29 እና 30 ቀን 2016 ዓ.ም



ገላና ወልደሚካኤል(ዶ/ር)

የስድስተኛ ክፍል ፈተና የሚሰጥ ሲሆን፤ ሰኔ 4 እና 5 ቀን 2016 ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል ፈተና እንደሚሰጥ አመልክተዋል፡፡ ሁለቱም ፈተናዎች የሚታረሙት በሀገር በቀል የፈተና ማረሚያ ሶፍትዌር መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ተፈታኝ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ



አቶ በየነ በሪሶ

የመደበኛ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ከማድረግ ባለፈ ተጨማሪ የቲቶሪያል ትምህርት ቅዳሜ እና እሁድ እየተሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀም ከኩረጃ የፀዳ ውጤት እንዲያመጡ አሳስበዋል፡፡

በተመሳሳይ የሲዳማ ክልል ምክትል ርእሰ መስተዳድር እና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በየነ በሪሶ በበኩላቸው፤ በክልሉ የስድስተኛ ክፍል ፈተና ግንቦት 29 እና 30 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲሁም የስምንተኛ ክፍል ደግሞ ሰኔ 4 እና 5 ቀን 2016 ዓ.ም ለመስጠት መታቀዱን አመልክተዋል፡፡

በክልሉ የስድስተኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ እስከ አሁን 51 ሺ ተማሪዎች መመዝገባቸውን ገልጸው፤በተመሳሳይ የስምንተኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ አሁን ድረስ ከ72 ሺ በላይ ተማሪዎች መመዝገባቸውን ጠቁመዋል፡፡

ተማሪዎች ለፈተና እንዲዘጋጁ የተለየ የዝግጅት ንቅናቄ እየተደረገ ነው ያሉ ሲሆን፤በተለይ የስድስተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና በክልል ደረጃ ሲሰጥ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተማሪዎች እና ወላጆች የስነ ልቦና ዝግጅት እንዲያደርጉ ቀደም ብለን ስንሰራ ቆይተናል ብለዋል፡፡ የፈተናው የህትመት ዝግጅት ቀደም ብሎ በመጀመሩ በተቀመጠለት ጊዜ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

# ሕልማቸውን እውን ያደረጉ ወጣቶች

**አስቴር ኤልያስ**

**ሐተታ**

በርቀት ሲታዩ በሥነ ሥርዓት የተሰደሩ የእህል ማከማቻ መጋዘኖች ይመስላሉ፡፡ ከቁጥራቸው ብዛት የተነሳ ያረፉበትን የመሬት ስፋት በካሬ ሜትር ይህን ያህል ነው ብሎ ለመገመት ይከብዳል፡፡ ወደስፍራው እየተጠጋን ስንመጣ ግን በአጭሩ የታጠቁ ወጣቶች ሰፋፊ መግቢያ ባላቸው በሮች አጠገብ ተፍ ተፍ ሲሉ ይስተዋላሉ። ግማሹ ቱታ፣ ገሚሱ ደግሞ ቁምጣ ብጤ አጥልቆ በተጣደፈ መንፈስ ከወዲህ ወዲያ ይላሉ፡፡

ወደ መጋዘኑ መሰል ትልቅ ቤት ሙሉ በሙሉ በተቃረብን ጊዜ የሥራ እድል ለተፈጠረላቸው ወጣቶች በሸገር ከተማ በገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ አማካይነት የተመቻቹላቸው ሼዶች መሆናቸውን ተረዳን፡፡ ይህን ያጤንነው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሥራ እድል ፈጠራ ቢሮ በጋራ በመሆን በሥራ እድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ የመስክ ምልከታን ለጋዜጠኞች ባስጎበኙበት ወቅት ነው፡፡

ወደ አንደኛው የከብቶች ማደለቢያ ሼድ በዘለቅን ጊዜ በመጀመሪያ ያስተዋልነው ነገር ቢኖር ሁሉም ከብቶች ይበሉ የነበረውን መኖ ለአፍታ ገታ አድርገው ትኩረታቸውን ወደ ሰፊው በር ማድረጋቸውን ነው፡፡

በሼዱ ውስጥ ያገኘነው አንድ ወጣት አቡ ሞገስ ይባላል፡፡ ወጣት አቡ፣ የአቡ፣ መገርቱና ጓደኞቻቸው ከብት ማደለብ ኀብረት ሽርክና ማኅበር አንዱ አባል ነው። እርሱ እንደሚናገረው፤ የሽርክና ማኅበሩን የመሰረቱት አምስት ሆነው ነው፡፡ ማኅበሩን ከመመስረታቸውና በገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ አማካይነት ተሰርቶ ሼዱ ሳይሰጣቸው በፊት አምስቱም በየፊናቸው የቀን ሥራ በመሥራት የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ይሞክሩ ነበር፡፡

እርሱ እንደሚለው፤ ሥራ ለሌለው ሰው በብዙዎች ዘንድ "ሥራ አጥ" የሚል ስያሜ ስለሚሰጥ አባባሉ ስሜቱን ይጫነዋል፡፡ ይህን ወደኋላ ኀታች መንፈስ ጥሎ ለመውጣት ደግሞ መስራት የግድ እንደሆነ ይገነዘባል፤ ይሁንና እንዴት የሚለው ነገር ግራ ሲያጋባው ይቆያል። ነገር ግን በመጨረሻ የገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ በማኅበር አደራጅቷቸው ሼዶችን ብቻ ሳይሆን ለመሰረቱት የእርባታ ዘርፍ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማት ጭምር በማሟላቱ ስራውን በትጋት ይያያዘዋል፡፡

"በአሁኑ ወቅት ሥራ አለኝ ብዬ ከቤቴ ስወጣ ከፍ ባለ ደስታ ውስጥ ሆኜ ነው" የሚለው ወጣቱ፣ ማኅበሩን ለመመስረት 300 ሺ ብር የግድ ይል ስለነበር ብሩን ለማሟላት ከዘመድ አዝማድና ራሳቸው ያጠራቀሟትን በመጠቀም እንደሆነ ይናገራል፡፡ ለማጠራቀም ግን ወጣትነትን ከሚፈታተኑ ነገሮች ጋር ትንቅንቅ በመፍጠር የነገን ሕይወት ዛሬ ላይ ቆሞ በማለም ካልሆነ የሚሞከር አይደለም ይላል፡፡ ሕልማችን ከብት ማደለብ ላይ የሚያበቃ አይደለም ሲል ጠቅሶ፣ ነገ ከራሳቸው አልፎ ሀገርን የሚጠቅም ጠንካራ ኢኮኖሚ መፍጠር ጭምር እንደሆነ ይገልጻል፡፡

አንድ በሬ እስከ 50 ሺ ብር ድረስ ይገዛል የሚለው ወጣቱ አቡ፣ ለማደለብ ደግሞ ቢያንስ አንድ ወር ቢበዛ ደግሞ እንደ ከብቱ ሁኔታ ስለሚለያይ ሶስት ወር ድረስ ሊሔድ እንደሚችል ያስረዳል፡፡ የደለበውን በሬ መልሰው የሚሸጡት ከ80 ሺ እስከ 100 ሺ ብር ድረስ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ ይህን እድል ያመቻቸላቸው መንግሥት በመሆኑም ድጋፍና ክትትሉን እንዳይለያቸው ጠቅሷል። በቀጣይ ከራሳቸው ጠቀሜታ አልፈው ለሀገራቸው ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት መሆን እንደሚሹ ገልጿል፡፡

ከዚያ ከሼዶቹ በአንደኛው ውስጥ ስንገባ ያዳምጥነው የሁለት ሺ ዶሮዎችን ድምጽ ነው፤ ከማል፣ መሃመድ እና ጓደኞቻቸው የዶሮ እርባታ ኀብረት ሽርክና ማኅበር ደግሞ



ፎቶ ሀዲስ አብርሀ

ወጣት አቡ ሞገስ

በእንቁላል ዶሮ ምርት የተሰማራ ነው፡፡ በዚህ ማኅበር ውስጥ ከተካተቱ ስድስት አባላት ውስጥ አንዱ የሆነው አብዱራሃማን አሕመድ እንደሚለው፤ ዶሮዎቹ ከአንድ ወር በኋላ እንቁላል መጣል ይጀምራሉ፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ለሶስት ሰው የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

ቀደም ሲል ሥራ አጥ ነበሩ፤ ክፍለ ከተማው በሰጣቸው ትልቅ እድል በመታገዝ ግን የስራ ባለቤት መሆን ቻሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ለስራቸው መብራትም ውሃም በመግባቱ አይቸገሩም፡፡ ክፍለ ከተማው በተለይ የስራቸውን ሁኔታ ለማየትና ለማበረታታት በቀን ሁለት ጊዜ እንደሚመጣም ያመለክታሉ፡፡

ማኅበሩን ያጠናከሩት በመጀመሪያ ከዘመድ አዝማድ ባገኙት 800 ሺ ብር አካባቢ ሲሆን፣ በቀጣይ ዶሮዎቹ ሁለት ሺ እንቁላል መጣል የሚጀምሩበት ጊዜ ቅርብ ነው ይላል፡፡ ይህ ለእነርሱ ትልቅ ተስፋ ሲሆን፣ ቀጣዩ ግባቸው ስራቸውን አሳድገው ለሀገር ትልቅ ነገር ማበርከት ጭምር ነው ሲል ይናገራል፡፡ ለዚህ ሁሉ ግን ትዕግስት መልካም ነው፤ የነገውን ሕይወት የተሻለ ለማድረግ ዛሬ ላይ



አብዱራሃማን አሕመድ

በተመቻቸው እድል በመጠቀም በትጋት መስራት የግድ እንደሚል ያስረዳል፡፡

ስኬታማነታቸው ሳይቋረጥ ይቀጥል ዘንድ ግን በአሁኑ ወቅት የዶሮዎች መኖ ከፍተኛውን ወጪ ስለሚወስድ ከዚህ ጋር ተያይዞ ትኩረት ቢሰጥበት ምርታማነት እንደሚቀጥል ነው የሚያስረዳው፡፡ አሁን ያሉበት ሼዶች ዙሪያው ቢታጠር የተሻለ እንደሚሆን አመልክቷል፡፡

የገላን ጉዳ ከተማ ለሥራ አጦቹ ወጣቶች የተሻለ ነገር ለማቅረብ ሼዶቹን በመስራቱ ወቅት በብዙ እንደደከመባቸው የሸገር ከተማ የገላን ጉዳ ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ዱጉማ ሙለታ ይናገራሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፤ 106 ሾዶች የተሰሩት ከዛሬ ሶስት ወር በፊት ነው፡፡ ሼዶቹን የሰጡት ለስራ አጡ ወጣት ሲሆን፣ በዘልማድ ያመርትና ያረባ ለነበረው አርሶ አደር ጭምር ነው፡፡

ሥራ አስኪያጁ እንደሚሉት፤ በማኅበር ለተደራጁ የሥራ እድል ተጠቃሚዎቹ ብድር በማመቻቸትም ስራቸውን ውጤታማ እንዲያደርጉ ይሻሉ፡፡

# ዩኒቨርሲቲው ሕጎችና መመሪያዎችን በአግባቡ እንዲተገብር ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚተዳደረው የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ዩኒቨርሲቲውን በገቢ መደገፍ እንዲችል የወጡ ሕጎችና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ ማመንጫ (ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) የሥራ አፈጻጸምን የሚመለከት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ ትናንት ተወያይቷል፡፡

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሺእመቤት ደምሴ(ዶ/ር)እንደተናገሩት፤ ኢንተርፕራይዞች በመጀመሪያ ሲቋቋሙ የዩኒቨርሲቲዎች አካል ተደርገው ነው፡፡ እንዲቋቋሙም ምክንያት የነበረው ኢንተርፕራይዞች የራሳቸውን ገቢ በማመንጨት ዩኒቨርሲቲውን በገንዘብ መደገፍ እንዲችሉ ታልሞ ነው፡፡

በ2012 ዓ.ም መንግሥት አሰራሩን በመፈተሽ ለቦርድ ተጠሪ እንዲሆኑ አድርጓል ያሉት ሰብሳቢዋ፤ ሆኖም ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መመሪያውን በመጣስ በኢንተርፕራይዙ የሚሰሩ ሥራዎችንም ሆነ የታዩ ክፍተቶችን በአመራር ቦርድ እንዲገመገም አለማድረጉ በኦዲት ሪፖርቱ ተመላክቷል ብለዋል፡፡



የሺእመቤት ደምሴ(ዶ/ር)

በዚህም ኢንተርፕራይዙ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ 80 በመቶ ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና አላማ ማስፈጸሚያ ማዋል ሲገባው እስካሁን ምንም አይነት ገቢ አለማስገባቱን ገልጸው፤ ዓመታዊ ሂሳቡንም መመሪያው በሚያዘው የፋይናንስ አመዘጋገብ ሥርዓት መሰረት እየሰራ አለመሆንን ተናግረዋል፡፡

ኢንተርፕራይዙ በአሁኑ ጊዜ ገቢ ከማስገኘት ወርዶ በኪሳራ ውስጥ እንደሚገኝ የተናገሩት ሰብሳቢዋ፤ በዚህም የወጡ ሕጎችና መመሪያዎችን ተከትሎ በመስራት ዩኒቨርሲቲውን በገቢ መደገፍ የሚችልበትን አሰራር መዘርጋት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ እንደገለጹት፤ ኢንተርፕራይዙ ጤናማ አሰራርን ተግባራዊ



ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ

በማድረግ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ የሚፈጥርበትን አሰራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

የወጡ ደንብና መመሪያዎች አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረጉ እንዳልሆነ በኦዲት ሪፖርቱ ማየት ተችሏል ያሉት ኦዲተሯ፤ ኢንተርፕራይዙ ገቢውን ማስፋት እንዲችል ያሉበትን ጉድለቶች ለይቶ መቅረፍ ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አያኖ ቦራሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢንተርፕይዙ ሲቋቋም ዩኒቨርሲቲውን በገንዘብ እንዲደግፍ ታስቦ ነው፡፡ ሆኖም በሂደት ያጋጠሙ የአሰራር ሥርዓት ችግሮች ነበሩ፡፡

ዩኒቨርሲቲው አሁን ላይ በኢንተርፕራይዙ የሚሰሩ ሥራዎችንም ሆነ የታዩ ጉድለቶች ዩኒቨርሲቲው በአመራር



ዶ/ር አያኖ ቦራ

ቦርድ ያስገመግማል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሆኖም ሂደቱ መጓተት የነበረበት በመሆኑ ኢንተርፕራይዙ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል ብለዋል፡፡

ኢንተርፕራይዙ ውጤታማ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች በመለየት አሁን ላይ የአዋጭነት ጥናት እንዲጠና ተደርጎ ወደ ሥራ ተገብቷል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህም የኢንተርፕራይዙን የገቢ ማመንጫ ዘርፎችን ማስፋፋት ላይ እንዲሁም ማጠናከር ላይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል ብለዋል፡፡

የሂሳብ ሥርዓቱ ላይም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች የቀረበው የኦዲት ግንኝትን እንደ ድክመት የሚወሰድ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ገልጸው፤የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ የሚወሰድ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡



አለባቸው ንጉሴ (ዶ/ር)

# አምራች ኢንተርፕራይዞች ከ24 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ገቢ አስገኙ

## - 1 ነጥብ 32 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ወጪ አድነዋል

**ሶሎሞን በየነ**

**አዳማ**፡- በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት አምራች ኢንተርፕራይዞች 14 ሺህ 190 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ 24 ነጥብ 51 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ገቢ ማስገኘታቸውን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አስታወቀ። ኢንተርፕራይዞቹም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከውጭ የሚገባ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ሀገሪቱ ታወጣ የነበረውን 1 ነጥብ 32 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ወጪ ደግሞ ማዳናቸውን ኢንተርፕራይዙ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የእቅድ አፈፃፀምና የቀጣይ የሥራ አቅጣጫዎች ላይ የተቋሙ ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ትናንት በአዳማ ከተማ የግምገማና የውይይት መድረክ አካሂዷል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አለባቸው ንጉሴ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ አምራች ኢንተርፕራይዞች 11 ሺህ 525 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ አቅርበው 24 ነጥብ 89 ሚሊዮን ዳላር ለማግኘት ታቅዶ፤ 223 ኢንተርፕራይዞች 14 ሺህ 190 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ 24 ነጥብ 51 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ገቢ ተገኝቷል።

የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ከተያዘው እቅድ አኳያ አፈጻጸሙ 98 በመቶ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመው፤ በዋናነት የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ የምግብና የመጠጥ፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶች፣ የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ወደተለያዩ ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢው እንደተገኘና 223 ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንደሆኑ አስረድተዋል።

ተቋሙ ከክልልና ከፌዴራል ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለአምራች ኢንተርፕራይዞች እያደረገ ባለው የተሟላ ድጋፍ የአምራች ኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ገልጸው፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት አምራች ኢንተርፕራይዞች 1 ነጥብ 78 ቶን ከውጭ የሚገባ ምርት በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ሀገሪቱ ታወጣ የነበረውን 1 ነጥብ 32 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ወጪ ማዳናቸውን ገልጸዋል።

በዚህም 1ሺህ 387 አምራች ኢንተርፕራይዞች ከውጭ የሚገባ ምርትን በሀገር ውስጥ በመተካት ሥራ ላይ በመሠማራት ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ አዲስ በተቋቋሙና በተጠናከሩ ነባር አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ለ138 ሺህ 922 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ ለ106 ሺህ 441 ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፈጠሩን ዋና ዳይሬክተሩ አክለው ገልጸዋል።

ከተያዘው እቅድ አኳያ አፈጻጸሙ 77 በመቶ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 61 ሺህ 220 በአነስተኛ እንዲሁም 45 ሺህ 221 በመካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች እንደሆነ ተናግረዋል።

የተቋሙ የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ከተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች ባሻገር የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አመራርና አባላት በተገኙበት ቀርቦ ግምገማና ውይይት ተደርጎበታል።

# ኤልሳልቫዶር በአፍሪካ ሁለተኛ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ልትከፍት ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

<ins>አዲስ አበባ</ins>፡- ኤልሳልቫዶር በአፍሪካ ሁለተኛ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ልትከፍት መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ የኤልሳልቫዶር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤሌክሳንድራ ሂል ቲኖኮ የተመራ ልዑካን ቡድን ትናንትና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴ ጋር ተገናኝተው በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ትብብር ዙሪያ መክረዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደገለጸው፤ ኢትዮጵያና ኤልሳልቫዶር በባለብዙ መድረኮች በሆነው በደቡብ ደቡብ ማዕቀፍ ትብብር በጋራ የሚሰሩባቸውን እድሎች ለማስፋትና ለማጠናከር ከስምምነት ደርሰዋል፡፡

ከውይይቱ በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ ነብዩ ተድላ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ኤልሳልቫዶር ያላቸውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ተስማምተዋል፡፡ ሁለቱ ሀገራት በባለብዙ መድረኮች ላይ በተለይ በደቡብ ደቡብ የትብብር ማዕቀፍ አብረው የሚሰሩባቸውን ሁኔታዎች እድሎች ለማስፋት ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

በተለይ በግብርና፣ በትምህርትና በስፖርት መስኮች ተባብረው ለመስራት በሚያስችሏቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሃሳብ ልውውጥ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

የኤልሳልቫዶር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤሌክሳንድራ በአዲስ አበባ የሁለት ቀን ቆይታ ይኖራቸዋል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በሚኒስትሯ የሚመራው ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ ጉብኝት እያደረገ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

ኤልሳልቫዶር ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያን ጉዳይ የምትከታተለው በሞሮኮ ባለው ኤምባሲዋ እንደነበር አውስተው፤ አሁን በአፍሪካ ሁለተኛ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ለመክፈት ወስናለች፡፡ ውሳኔውን ተግባራዊ የሚያደርግ ልዑካን ቡድን በቅርቡ ወደ አዲስ አበባ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ነብዩ ገለጻ፤ የኤልሳልቫዶር በአዲስ አበባ ኤምባሲዋን ለመክፈት የምታደርገው ጥረት የኢትዮጵያ መንግሥት ሙሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴ አረጋግጠዋል። ከኤልሳልቫዶር ጋር በተለያዩ መስኮች የኢትዮጵያ መንግሥት አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑንም አሳውቋል፡፡



ፎቶ ሐዲስ አብርሃ

# ለፋሲካ በዓል ሸማቹ በነጻነት እንዲገበያይ ጥምር የፀጥታ ግብረ ኃይሉ ወደ ሥራ ገብቷል

**ታደሠ ብናልፈው**

<ins>አዲስ አበባ</ins>፡- በአዲስ አበባ ከተማ ለፋሲካ በዓል ነዋሪዎች በግብይት ማዕከላት በነጻነት እንዲገበያዩ እና የተለያዩ ወንጀሎችን አስቀድሞ ለመከላከል ጥምር የፀጥታ ግብረ ኃይሉ ወደ ሥራ መግባቱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ በፋሲካ የበዓል የግብይት ሥርዓት ላይ የፀጥታ ችግር ሳይፈጠር ነዋሪዎች በሰላም እንዲገበያዩ ከወዲሁ ስምሪት ተደርጎ እየተሠራ ነው፡፡

በመዲናዋ ለፋሲካ በዓል በተለያዩ ቦታዎች ግብይቶች ይፈፀማሉ፤ እነዚህ ግብይቶች ላይ ሊፈፀሙ የታሰቡ የተለያዩ ወንጀሎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ነዋሪዎች በሰላም እንዲገበያዩ ጥምር የጸጥታ ግብረ ኃይሉ ወደ ሥራ ገብቶ እየተሠራበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመዲናዋ በመደበኛና በበዓላት ጊዜ ማህበረሰቡ ግብይት የሚፈጽምባቸው በርካታ የገበያ ማዕከላት መኖራቸውን ገልጸው፤ የፋሲካን በዓል አስታኮ በእነዚህ የገበያ ማዕከላት ላይ ምንም አይነት የወንጀልና የፀጥታ ችግር ሳይፈጠር ሸማቹና አምራቹ በሰላም



ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ

እንዲገበያይ ወንጀልን አስቀድሞ የመከላከል ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡

የመዲናዋ ነዋሪዎች የፋሲካን በዓል ለማከበር በሚያደርጉት ግብይት ላይ በሌቦችና በነጣቂዎች ወንጀል እንዳይፈፀምባቸውና ባሉት የገበያ ማዕከላት በነጻነት እንዲሸምቱ በጥምር የፀጥታ ግብር ኃይሉ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በከተማዋ በመደበኛ የግብይት ሥርዓትም ሆነ በዓላት ጊዜ ሕገ ወጥ የገንዘብ ልውውጥ፤ በምርቶች ላይ በአድ ነገር መቀላቀል፤ እቃዎች ላይ ከፍተኛ ዋጋ መጨመርና የአላግባብ መከዘን ወንጀሎች በቁጥጥር ሥራ ላይ እንደሚያጋጥሙ ጠቅሰው፤ እነዚህን ወንጀሎች በመጪው የፋሲካ በዓል እንዳይፈጸሙ አስቀድሞ ለመከላከል ጥምር የጸጥታ ኃይል ስምሪት ወስዶ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

በገበያ ማዕከላት አምራቹ ከሸማቱ ጋር የሚያደርገው ግብይት ሰላሙ የተጠበቀ ለማድረግ ሕግ የማስከበር ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ያለው ሥራም እስካሁን ተጨባጭ የሆነ ውጤት አስገኝቷ፤ ለዚህ ውጤትም ማህበረሰቡም ትልቁን ሚና እየተጫወተ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የዘንድሮውን የፋሲካ በዓል ማህበረሰቡ ያሰበውን ምርትና ሸቀጥ በሰላም ገብይቶ እንዲመለስ ወንጀልን አስቀድሞ የመከላከል ሥራ ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

በተያዘው ዓመት የአደባባይ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ስኬታማ ሥራ መሠራቱን ያወሱት ወይዘሮ ሊዲያ፤ በመጪው እሁድ የሚከበረው የፋሲካ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ መጠነ ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ተግባር ተገብቷል ብለዋል፡፡

በዓላትን ምክንያት በማድረግ በምርቶች ላይ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪና ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አካላትን ለመቆጣጠር እየተሠራ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ የፋሲካ በዓልም በሰላም ተከብሮ እንዲያልፍ ከማህበረሰቡ ጋር ሰላም የማስከበር ቅንጅታዊ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# በያዝነው ዓመት ሦስት ሺህ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የትግራይ መስህቦችን ጎብኝተዋል

**ሔርሞን ፋቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ትግራይ ክልል በ2016 ዓ.ም ሶስት ሺ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ማስተናገዱን የክልሉ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

በቢሮው የብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክተር አቶ የማነ ገድሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ከጦርነቱ በፊት ከ80 እስከ 90 ሺ ድረስ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች እንዲሁም ከሁለት እስከ ሶስት ሚሊዮን ድረስ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች የትግራይ የቱሪዝም መስህቦችን ይጎበኙ ነበር፡፡

አሁን ላይ እስከ ሶስት ሺ ገደማ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች መምጣታቸውን ገልጸው፤ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ስንመለከት በተለያዩ በዓላት እና ፌስቲቫሎች የትግራይ ወጣቶች በአካባቢያቸው እየተደራጁ በተለይ ቅዳሜ እና እሁድ ተራራ በመውጣት እና የተለያየ ዝግጅት በማድረግ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች እና ጥበባት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑን ገልጸው፤የቱሪዝም መስህብ የሚሆኑ ቦታዎች እየተስፋፉ መሆኑን እና ወደ ትግራይ የሚመጡ ቱሪስቶች ቆይታቸውን ለማራዘም ተስፋ የሚሰጡ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ቀደም ሲል የቱሪዝም እንቅስቃሴ በአክሱም አካባቢ ብቻ መኖሩን የገለጹ ሲሆን፤በአሁኑ ወቅት ግን ወደ ገረዓልታ፣ጉሎመኸዳ፣ጋንታ አፈሹም፣አፅቢ እና ውቅሮ አካባቢዎች የሚመጡ ቱሪስቶች መኖራቸውን እና ጎብኚዎቹ የቆይታ ጊዜያቸው እንዲራዘም እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

የቱሪዝም መስህብ ለጎብኚዎች የተመቸ እና የተጠበቀ ለማድረግ የቱሪስቶች መነሻ እና መዳረሻ ቦታዎች ሰላማዊ እንዲሆን በፀጥታ አስከባሪዎች የተጠናከረ ጥበቃ ይደረጋል ያሉ ሲሆን፤የሰላም ስምምነት ከተደረገ ወዲህ በቱሪስቶች ላይ የደረሰ አንድም ችግር አለመኖሩን ጠቅሰው፤ለዚህ ደግሞ ህብረተሰቡ ለቱሪዝም ያለው ግንዛቤ ከፍተኛ ስለሆነ ነው ብለዋል፡፡

የቱሪዝም መሰረተ ልማት በተመለከተ ገረዓልታ ላይ በፌዴራል መንግሥት እየተሰራ የሚገኘው የገበታ ለሀገር አካል የሆነው ሎጅ በጥሩ ሂደት ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም ገረዓልታ እንደ ተጨማሪ የቱሪዝም መስህብ ‹‹ምርጥ የቱሪዝም መንደር›› በመሆን ተመራጭ እንዲሆን ለውድድሩ የሚመጥኑ የዶክሜንተሪ ሥራዎች፣ ፅሑፎች፣ፎቶ ግራፍ እና ቪዲዮ ተዘጋጅተው ወደሚመለከተው አካል መላኩን የገለፁ ሲሆን፤ገረዓልታ በዓለም ከሚገኙ ተመራጭ የቱሪዝም ቦታዎች ዝርዝር ሲካተት በኢኮኖሚ ከሚያስገኘው ጥቅም በላይ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

# ጤናማ ዜጋና ጽዱ ከተማን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አለመቁጠርና የመጸዳጃ ቤቶች እጥረት አንዳንዶችን በውጪ እንዲጸዳዱ ገፊ ምክንያት እንደሆናቸው ይነገራል፡፡ ይህ ደግሞ የሀገርን ገጽታ ከማበላሸት በዘለለ በርካታ ዜጎችን ለበሽታ የዳረገ ጉዳይ ሆኗል፡፡

ስለ ጽዳት ያለው ሸውራራ ግንዛቤ እንዲቃናና በቂ የሆነ መጸዳጃ ቤት ተሰርቶ ዜጎች ጤናቸው እንዲጠበቅ እንዲሁም ጽዱና አረንጓዴ ከባቢን ለመፍጠር “ጽዱ ኢትዮጵያ” የተሰኘው ሀገር አቀፍ ንቅናቄ ተጀምሯል፡፡ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ በርካቶች በንቅናቄው ተሳታፊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ንቅናቄውን ያስጀመሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ትኩረት ከተሰጠባቸው ነገሮች አንዱ ጽዱና አረንጓዴ ከካባቢ መፍጠር ነው፡፡ ክብር ያለው የንጽህና ባህል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ክብር ያለው የንጽህና ባህል ማለት በተገቢው ቦታ ክብርን ጠብቆ መጸዳዳት ሲሆን፤ ለዚያ ሥርዓት ማበጀትና የመጸዳጃ ቦታ መገንባት አስፈላጊ ሥራ ነው፡፡

“ሥርዓቱን በተመለከተ በማስተማርና ህግ በማስከበር ልናመጣውና ልናሳድገው እንችላለን” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የመጸዳጃ ቦታውን መገንባት ደግሞ ተጠባቂ ሥራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የግንባታውም ተግባር ቶሎ መጀመር አለበት በማለት፤ ንቅናቄው የመጸዳጃ ቤቶችን ተደራሽ ማድረግና ክብርን ጠብቆ የመጸዳዳት ባህልን ለማዳበር እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ በመልካም ተግባር ላይ የሚሳተፉ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች ከተማዋን ጽዱ፣ አረንጓዴና ውብ ለማድረግ እንዲተባበሩ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

“ይህ ንቅናቄ የሥራ እድል ይፈጥራል፡፡ ጤናችንን እንድንጠብቅ በእጅጉ ያግዛል፡፡ የኑሮ ዘዬችንን ያዘምናል፡ ፡ በከተማችን በርከት ያሉ የመጸዳጃ ቤቶች መገንባት ባለን መሻት የዚህ ዓላማና ሃሳብ ተጋሪ የሆናችሁ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች በገንዘብ አሊያም መጸዳጃ ቤቶቹን በመገንባት ከጎናችን እንድትቆሙ እየጠየቅኩ በተባበረ ክንድ ከተማችንን እናስውብ፣ እናጽዳ የኑሮ ዘዬአችንን እንቀይር ሥልጣኔን ለልጆቻችን እናውርስ” ሲሉ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንቅናቄውን ያበሰሩት፡፡

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ እንደሚሉት፤ ባለፉት ዓመታት በጤና ሴክተር ውስጥ ሲሰራባቸው ከነበሩ ጉዳዮች ውስጥ የግልና የአካባቢ ንጽህና አንዱ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ማህበረሰቡንና የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን በማሳተፍ አካባቢን ጽዱ ማድረግ ከዛም አልፎ ውጪ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በማለት የተለያዩ ንቅናቄዎች ተደርገዋል፡፡ በተወሰነ መልኩ ለውጦች ታይተዋል፡ ፡ ነግር ግን በሚፈለገው ደረጃ የሚፈለገው የአካባቢ ጽዳት እንዲሁም የባህሪ ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡ ክብሩን ጠብቆ የሚጸዳዳ ዜጋ መፍጠር ላይ ሰፊ ክፍተት ተስተውሏል፡፡

የአካባቢ ንጽህና ከ50 በመቶ በላይ ለሚሆኑ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መንስዔ ነው ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ የአካባቢ ጽዳትንና የግል ንጽህናን በመጠበቅ በርካታ በሽታዎችን፣ ሞትንና አካል ጉዳተኝነትን መቀነስ እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ በኢትዮጵያ በርካታ በሽታዎች ከንጽህና ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስለሆነ፤ ይህ ተግባር አሁንም በቀዳሚነት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ብለዋል፡ ፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሰሞኑን “ጽዱ ኢትዮጵያ” በሚል መሪ ሃሳብ የጀመሩት ንቅናቄ በተለይ ንጽህናቸው የተጠበቁ መንገዶችን እንዲኖሩ ለማድረግ፤ ዜጎች ውጭ ላይ ከሚጸዳዱ መጸዳጃ ቤቶችን በመገንባት ሰፋፊ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት የሚረዳ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የተለያዩ መጸዳጃ ቤቶችን በመገንባት ማህበረሰቡን ጤናውን እንዲጠብቅ ለማድረግ ጉልህ ሚና ያለው እንደሆነም አንስተዋል፡፡

ንቅናቄው ለጤና ሴክተሩ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ነው በማለት፤ “በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደሚባለው ንቅናቄው ጽዱ ከባቢን ከመፍጠር ባሻገር፤ ግንባታውን ለማከናወን አጋር ድርጅቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ሰፊው ማህበረሰብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሀብት የሚያሰባስቡበት ብዙ ሥራዎችን መስራት እንደሚቻል ማሳያ የሚቀርብበት መልካም አጋጣሚ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ዜጎች በመንገድ ላይ ሲጸዳዱ ይስተዋላል ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ ንቅናቄው ኩሩና ክብሩን ጠብቆ የሚጸዳዳ ዜጋ ለመፍጠር እንደሚያስችልም ጠቅሰዋል፡፡ በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ በርካታ ዜጎቿ ውጭ ላይ ይጸዳዳሉ ከሚባሉት ሀገራት ተርታ ውስጥ የምትሰለፍ እንመሆኗ ንቅናቄው ይህንን በእጅጉ የሚቀንስ ስለመሆኑም አንስተዋል፡፡

ዶክተር ደረጀ፤ በንቅናቄው የሚሰራው ሥራ የባህሪ ለውጥ ለማምጣትና የበሽታ ምንጭን ከመቀነስ አንጻር ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ውጭ ላይ መጸዳዳት አካባቢን የሚበክልና ክብርምም የማይገልጽ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ይልቁንም መርዛማ ኬሚካሎችን በማመንጨት በሽታን በማስተላለፍ በተለይ ሕፃናትን ለችግር የሚዳርግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ንቅናቄው ለብቻው የሚቆም እንዳልሆነ፤ እንደ ሀገርም ከታሰቡ ትልልቅ ጉዳዮች ጋር ተሳስሮ የሚተገበር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ውጭ ከመጸዳዳት ይልቅ አካባቢዎችን ነጻ ማድረግ እንዲሁም አካባቢን ማጽዳት ተብሎ የተቀመጠውን እቅድ የሚደግፍ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ጋር ተመጋጋቢ የሆነ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የጽዳት ጉዳይ መንገዶች ሲሰፉ ከተሞችን ምቹና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮ ተስማማሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ከሚሰሩ ኢንስትመንቶች ጋር ተሰናስሎ የሚተገበር መሆኑንም አንስተዋል፡፡

በግል ደረጃ መጸዳጃ ቤት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ህዝብ በሚበዛባቸው፣ ገበያ ቦታዎች፤ የትራንስፖርት ሥፍራዎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አካባቢዎች በርካታ መጸዳጃዎችን በመገንባት ማህበረሰቡ እንዲገለገል ያደርጋል ነው ያሉት፡፡ ለዚህም የተጀመረው ሀገር አቀፍ ንቅናቄ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትና ህዝቡ ለዚህ አቅሙ በፈቀደው መጠን ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ረቂቅ ሠነዱ ሀገራዊ ልማትና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ፡፡

በብሔራዊ የኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ ረቂቅ ሠነድ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ በትናትናው ዕለት ተካሂዷል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ብሔራዊ ኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ ሠነድ የዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥራ እድል ለመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪን ለማሳደግና ዓለም አቀፍ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ልማትን የማረጋገጥ ዓላማ አለው፡፡

ኢትዮጵያ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግዷን ለማሳደግ ኢ-ኮሜርስ ላይ በቁርጠኝነት እየሰራች መሆኗን ጠቅሰው፤ረቂቅ ስትራቴጂኪ ሠነዱ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ለመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

የኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ ዘርፉ የሕግ ማዕቀፍ ኖሮት ተወዳዳሪ ከማድረግ ባሻገር የዲጂታል ኢትዮጵያን ሽግግር ለማሳለጥ እንደሚረዳም አመላክተዋል፡፡ መንግሥት የንግዱን ምህዳር በማስፋት የገበያ ሥርዓቱን እንዲዘምን የተለያዩ የሕግ ማሻሻያዎችን እያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በቂ የኢ-ኮሜርስ የሕግ ማዕቀፍ ባለመዘጋጀቱ ማህበረሰቡ ከዘርፉ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ሳያገኝ ቆይቷል ነው ያሉት፡፡

የስትራቴጂ ሰነዱ የዲጂታል ኢትዮጵያ አካል ሲሆን መንግሥት በልዩ ትኩረት እንደሚያስፈጽመው የጠቆሙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለውጤታማነቱ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባልም ብለዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስትሩ ገብረመስቀል ጫላ በበኩላቸው፤ ኢ-ኮሜርስ የንግድ ተቋማት ጊዜና ቦታ ሳይገድባቸው ከተጠቃሚዎች ጋር በኦንላይን እንዲገናኙ በማድረግ የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲሳለጥና የሥራ ፈጣሪዎች በሁሉም ስፍራ እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡

እንደ አቶ ገብረመስቀል ገለጻ፤ ስትራቴጂው የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ የተነደፈ ነው፡፡

ኢ-ኮሜርስን በመጠቀም የሀገር ውስጥ ግብይቶችን ማዘመን፣ የወጪ ንግድን ማመቻቸትና ጠንካራ የሎጂስቲክስ ሥርዓት እንዲፈጠር ስትራቴጂው ጥቅም የጎላ ነው ብለዋል፡፡

ስትራቴጂው በቶኒቢሊየር ኢንስቲትዩት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በጋራ የተዘጋጀ መሆኑም ተገልጿል።

በመድረኩ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የልማት አጋር አካላትና የግል ሴክተር ተወካዮች ተገኝተዋል።

# “የኢትዮጵያ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን በሚመራው ሥራ ምክክር እና የእርቅ ሰላም ፍላጎታችን እና ተምኔታችን ማጠንጠኛ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ ብሎም ወጣቶችን በማብቃት ኢትዮጵያ ሁለት ሚሊዮን አዳዲስ ሥራዎችን ለመፍጠር ውጥን መያዟን ተናግረዋል።

አረንጓዴ አሻራን በመሰሉ ሰፊ ንቅናቄዎች እንዲሁም ከአካባቢ ጋር የተስማማ የኤሌክትሪክ ኃይልን ለሁሉም በማዳረስ፣ የዲጂታል ሽግግር እና የተፈጥሮ ከባቢን የመንከባከብ ተግባራት ለመከወንም ትኩረት ሰጥታለች ሲሉ ተናግረዋል።

በመድረኩ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ለአህጉሩ ድጋፉን እንዲያጠናክር ጥሪ አቅርባለች።

ጉባኤው ለአፍሪካ ልማት የገንዘብ ድጋፍና ቀዳሚ የትኩረት መስኮችን ለማመላከት እንዲሁም በጉዳዩ ላይ አፅንዖት ለመስጠት ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

የገንዘብ ድጋፍ አቅራቢዎች በ21ኛው የማኅበሩ ዘመን ድጋፋቸውን ለመጨመር በፅኑ እንዲያጤኑ የማሳሰብ አላማ ያነገበ መድረክ መሆኑም ተመላክቷል።

የሚቀርቡ ድጋፎች የአፍሪካን የልማት ተግዳሮቶችና መልካም እድሎች በተገቢው መንገድ ለማስተናገድ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል።

# “በኮሪደር ልማቱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በኮሪደር ልማት ምክንያት የተነሳውን ጽርሃ ሚኒሊክ (በተለምዶ መሀሙድ ሙዚቃ ቤት) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሕንጻ የመልሶ ግንባታ ሥራ አስጀምረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ የግንባታ ሥራውን ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለጹት፤ በኮሪደር ልማቱ የተነሱ የቤተክርስቲያን ሀብቶችን መልሶ የማልማቱ ሥራ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በትብብር እየተሰራ ነው፡፡ ሰላምና ልማት ለአንድ ሀገር ወሳኝ ነው ያሉት ብጹዕነታቸው፤በከተማው በኮሪደር ልማት የሚሰሩ የልማት ሥራዎች አስደሳች ቢሆንም ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸው ቦታ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

ብጹዕ አቡነ ማቲያስ አክለውም ዜጎች መውደቂያ እንዳያጡ ታሳቢ ተደርጎ የሚሰራ ልማት የሚደገፍ ነው ያሉ ሲሆን፤ በልማቱ የተነሱ ቦታዎች ለምትተው እንዲመለሱም ጠይቀዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ለሀገር የምትጸልይ በመሆኗ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ያሉት ፓትርያርኩ፤በመልሶ ማልማቱ የሚሰራው ሁለገብ ሕንጻ በጥራትና በተያዘለት ጊዜ ተሰርቶ ለቤተ-ክርስቲያን ማስረከብ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ቅዱስ ፓትርያርኩ ገለጻ፤ ሕንጻው ሲፈርስ ጥናት ተደርጎ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመነጋገር የሚበጀውን የጋራ ውሳኔ ተወስኖ ነው፡፡ ከዚህ ወጪ በሌሎች ቦታዎች በኮሪደር ልማቱ የተነሱ የቤተ-ክርስቲያኑ ሀብቶች ለምትተው ተመላሽ መደረግ አለባቸው ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ የቀድሞ ሕንጻው ሲፈርስ ከቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደርና ከብጹሃን አባቶች ጋር ንግግር ተደርጎ ነው ያሉ ሲሆን፤ በመልሶ ማልማት ግንባታው የኮሪደር ልማቱ በሚፈቅደውና ለአካባቢው ተጨማሪ ድምቀት በሚሆን መልኩ ይገነባል ብለዋል፡፡

ወይዘሮ አዳነች አክለውም፤ በአካባቢው ንብረትነቱ የቤተክርስቲያን ሃብት የነበረው ግራውንድ ፕላስ አራት ሕንጻ ማንሳት ያስፈለገበት ምክንያት ከሌሎች የልማት ሥራዎች ጋር ለማሳለጥና በተሻለ ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ነው፡፡ በመልሶ ግንባታው ግራውንድና አንድ ቤዝመንት እንዲሁም ባለ 4 ወለል ህንጻ ሙሉ በሙሉ በከተማ አስተዳደሩ ወጪ ይገነባል ያሉ ሲሆን፤ ግንባታውም በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ወራት እንደሚጠናቀቅ አስረድተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ አዳነች ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የከተማ ፕላንና ልማት እንዲጠበቅ እንዲሁም ከተማዋ እንድትለማ ዲዛይኑ እንዲተገበር በርካታ ትብብር አድርጋለች፡፡

የከተማዋን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ በአምስት ኮሪደሮች ልማት እየተከናወነ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤በተለይ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ከተገነባ ወዲህ ሌሎችም ቅርሶችና ልማቶች ተናባቢ እንዲሆኑ እንዲሁም አንድ ላይ እንዲጎበኙ ለማድረግ እንዲቻል እየታደሱ ይገኛሉ ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የ«ፅዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና» ቴሴቶንን በመቀሳቀል፣ ፅዱ ኢትዮጵያን እውን እናድርግ

ዜጎች በንጹህ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብት አላቸው፡፡ ይሄ መሆኑ ደግሞ የሰው ልጆች በአካባቢ መቆሸሽና ብክለት ምክንያት ከሚፈጠርባቸው ዘርፈ ብዙ ችግር እንዲጠበቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በተለይ ንጹህ አካባቢ ላይ የሚኖሩ ሰዎች ከቆሻሻ ጋር ተያይዞ የሚከሰት በሽታና ወረርሽኝ የተጠበቁ ናቸው፡፡

በዚህ ረገድ በከተሞች የሚታየው የጽዳት ሁኔታ እንደ ሀገር ካለን የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ጋር ተዳምሮ፣ ዜጎች ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ንጹህ ከባቢ የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብትን የማጣት ብቻ ሳይሆን፤ ከፍ ላለ የጤና ችግር ሲዳረጉ ማየት የተለመደ ሆኗል።

በተለይ በከተሞች አካባቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝብ ቁጥር መጨመር እና የከተሞች መስፋፋት፤ ቆሻሻ አስተዳደር ሥርዓቱ ላይ የራሱን ችግር ይዞ መምጣቱ አልቀረም፡፡ ምክንያቱም ከተሞች በሰፉ እና ነዋሪዎቻቸውም በጨመረ ቁጥር፤ ከፍ ያለ ቆሻሻን የማምረት አቅም ይኖራቸዋል፡፡

ይሄ የሚመረት ቆሻሻ ደግሞ በአግባቡ ካልተወገደ እና ነዋሪዎችም በተገቢው መልኩ ቆሻሻን ካላስወገዱ፤ ከተሞች ከፍ ያለ የቆሻሻ ክምችትን ማስተናገዳቸው አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ ላይ መዲናይቱን አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች የመንገድ ዳርቻዎች ላይ የቆሻሻ ክምችት የሚታየው፡፡

ይሄ ደግሞ በአንድ በኩል የዜጎችን ጤና የሚያውክ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለዓይን የማይማርክ፤ ለአፍንጫም መልካም ያልሆነን ሽታ የሚጋብዝ አካባቢን የሚፈጥር ነው፡፡ እናም ችግሩ ከከተሞች ነዋሪዎች ባሻገር አልፎ ሂያጅ መንገደኛን፤ ውሎ አዳሪ እንግዳን ምቾት መንሳቱ እሙን ነው፡፡

ይሄን እግር ተገንዝቦ መፍትሄ ከመስጠት አኳያ ላለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡ ፡ በተለይ ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ማግስት ከቤት እስከ አደባባይ፤ ከከተማ እስከ ሀገር የሚዘልቅ ውብና ንጹህ፣ ማራኪና ጽዱ የሆኑ አካባቢዎችን ለመፍጠር እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዚህ ረገድ አዲስ አበባን ብቻ ብንወስድ፣ ለዓመታት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሆነው ታጥረው የቆዩ ቦታዎችን (ለምሳሌ፣ የሸራተን ማስፋፊያ እና ፒያሳ ማዘጋጃ ቤት አጠገብ የሚገኘው ቦታ) መቀየር ተችሏል፡ ፡ በዚህም የበርካታ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የአደገኛ ተግባራት መፈጸሚያ የነበረውን የሸራተን ማስፋፊያ፣ በገበታ ለሸገር ፕሮጀክት "ወዳጅነት አደባባይ" በሚል ታቅፎ አሁን ላይ ውብና ሁሉም ሄዶ ሊዝናናበት ወደሚናፍቀው ይዘት ተቀይሯል፡፡

በተመሳሳይ የፒያሳን ገጽ በብዙ መልኩ ሲያጠይም የኖረው እና የብዙ ቆሻሻና ክፉ ተግባር መድረክ ሆኖ የኖረው ቦታ፤ ዛሬ ላይ የዓድዋ ታሪክና ጀግኖች በክብር የሚታሰቡበት ሕያው ሙዚየም ተሰርቶበት፣ እንደ ሀገርም፣ እንደ አህጉርም የብዙዎች የኩራት ምንጭ፤ የቱሪዝም ሀብት መሆን ችሏል፡፡

እነዚህ እና መሰል ከተማንም ሀገርንም ውብ እና ጽዱ የማድረግ ተግባራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ እና የተለያዩ ከተማም ሆነ ሀገር አቀፍ የሆኑ ችግሮችን እልባት በሚሰጡበት አግባብ እየተቀረጹና እየተተገበሩ ይገኛል፡፡ በዚህ በኩል፣ ከቆሻሻ አወጋገድ እና የመጸዳጃ ቤት ችግር ጋር የተያያዙ ሥራዎች ይገኙበታል፡፡

በዚህም በተለይ በከተሞች ያለውን የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ከማዘመን ጀምሮ፣ ነዋሪዎች በእንቅስቃሴ ላይ እያሉ ለሚገጥማቸው የመጸዳጃ ቤት ችግር መፍትሄ እስከ መስጠት የዘለቁ መልካም ጅምሮች ታይተዋል፡ ፡ ውጤት እየተገኘባቸውና ውብና ጽዱ አካባቢዎች ሲፈጠሩም ማየት ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ እንደ ሀገር ካለን ከፍ ያለ ስምና ዝና፤ እንደ አዲስ አበባም ከፍ ያለ የዲፕሎማቲክ መዲናነት፤ ይሄን መልካም ጅምር ማላቅና ኢትዮጵያንም ንጹህ ማድረግ፤ አዲስ አበባንም እንደ ዲፕሎማቲክ መዲናነቷ ማስዋብና ለነዋሪዎቿም፣ ለእንግዶቿም ማራኪ ማድረግ የተገባ ነው፡፡

በዚህ ረገድ እንደ ቀደሙት ድንቅ አፈጻጸም እንደታየባቸው ውጥኖች ሁሉ፤ አዲስ አበባን ውብና ማራኪ፣ ኢትዮጵያንም ጽዱና ለዜጎቿ የምትመች ለማድረግ የ"ጽዱ ኢትዮጵያ" ፕሮጀክት ንቅናቄ ተጀምሯል፡፡ ይሄ ፕሮጀክት ደግሞ ከተሞችን ንጹህና ውብ በማድረግ ለነዋሪዎቻቸው የተመቹ በማድረግ ሂደት ውስጥ፤ ኢትዮጵያን በልኳ የሚገልጽ የንጽህና መልክ ማላበስን ግቡ ያደረገ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይሄ ታላቅ ውጥን በመንግሥት አቅም ብቻ ከዳር የሚደርስ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሁሉንም ዜጎች ትብብርና ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይሄንኑ እውነት የተገነዘቡ ቅን ኢትዮጵያውያንም ንቅናቄውን እየተቀላቀሉ ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ ከዜጎች የሚጠበቅ መልካም ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀናት ይሄንኑ "ፅዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና" ቴሌቶንን በመቀላቀል፣ ፅዱ ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ኃላፊነታችንን እንወጣ!!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በሕፃናት አስተዳደግና ሰብዕና ቀረጻ ላይ የማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ

**ኢያሱ መሰለ**

እያንዳንዱ ሰው ወደዚች ምድር በሚመጣበት የእንግድነት ዘመኑ ከለቅሶ ያለፈ እራሱን የሚገልጽበት ድምጽ/ቋንቋ የለውም፤ በተለይም ከሁለት እስከ ሦስት ዓመት እድሜው እሳትና ውሃን እንኳን ለይቶ አያውቃቸውም። ሰው ሙሉሰው በሚባል ደረጃ ላይ የሚደርሰው ከሕፃንነቱ ጀምሮ በወላጆቹና በአካባቢው ማህበረሰብ ድጋፍና ክትትል እየተደረገለት እያንዳንዱን ዝግመተ ለውጥ አልፎ ክፉና ደጉን ለመለየት በሚያስችል ቁመና ላይ ሲደርስ ወይም እርሱም እንደ ወላጆቹ ለኃላፊነት ሲበቃ ነው።

በሕፃናት አስተዳደግና ሰብዕና ቀረጻ ሂደት ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ቤተሰብ ነው ቢባልም ትምህርት ቤቶችና የአካባቢው ማህበረሰብም የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። እነዚህ ሦስት ባለድርሻዎች ሕፃናት ወደ ሙሉ ሰውነት በሚያደርጉት ጤናማም ሆነ ጤናማ ያልሆነ ሽግግር ውስጥ ዐሻራቸውን ማሳረፋቸው የማይቀር በመሆኑ በልጆች አስተዳደግ ወይም በሚይዙት ሰብዕና ተወዳሽም ተወቃሽም መሆናቸው የማይቀር ነው።

የሕፃናት አዕምሮ የጻፉበትን ሁሉ የሚቀበል ነጭ ወረቀት ነው የሚል ተለምዷዊ አባባል አለ። አባባሉ እውነት ነው። ሕፃናት እድሜያቸው ለአቅመ ትምህርት ከደረሰ በኋላ ያዩትን ወይም የሰሙትን መጥፎም ይሁን ጥሩ ነገር በአዕምሯቸው መዝግበው የመያዝ ተሰጥኦ አላቸው። ገና ክፉና ደጉን መለየት የሚያስችል እድሜ ላይ ባለመድረሳቸው ጉዳትና ጥቅሙን አያመዛዝኑም። የሚስፈልጋቸውን ብቻ ወስደው የማያስፈልጋቸውን የመተው ልምድ የላቸውም። ይልቁንም የሰሙትን እና ያዩትን ሁሉ አግበስብሰው ለመያዝ ይሞክራሉ እንጂ።

ታዲያ የወላጅ፣ የጎረቤት፣ የመምራን ወይም የታላላቆቻቸው ድጋፍና እገዛ የሚያስፈልጋቸው በዚህን ጊዜ ነው። ይሄ ጥሩ ነው ቀጥሉበት፤ ይሄ መጥፎ ነው፤ አይጠቅማችሁም ተውት፤ እያለ ቀናውን ሁሉ የሚያመላክታቸውና ክፉውን አቅጣጫ የሚያስተዋቸው መንገድ መሪ ያስፈልጋቸዋል። ከጥንት ጀምሮ ትውልድ ያለፈበት መንገድም ይሄው ነው። በየዘመኑ ‹‹ሀይ የዛሬ ልጆች!›› እየተባልንም ቢሆን ለዘመናት ያሳለፍነው የሕፃናት አስተዳደግ ባህላችን ይህንን መንገድ የተከተለ እንደነበር በተለይም በእድሜ ከፍ ያልን ሰዎች የምናውቀው ሐቅ ነው።

ሕፃናት ልክ እንደ ችግኝ ናቸው። ችግኝ እንክብካቤና ክትትል ይፈልጋል፤ ከለላና ጥበቃ ይደረግለታል፤ ውሃ ይጠጣል፤ ጎብጦ እንዳያድግም ይቃናል። ሕፃናትም እንዲሁ ናቸው፤ እንክብካቤን ይሻሉ፤ በተለይም ሰብዕናቸው የተበላሸ እንዳይሆን ገና በለጋ እድሜያቸው በምክር፣ በተግሳጽ አንዳንዴም በቁንጥጫ ፈር እንዲይዙ ይደረጋል። በእያንዳንዱ ዘመን ያለ ልጅ በአባቶቹ እግር ተተክቶ የሀገሩ ተረካቢ እንዲሆን በሥነ-ምግባር ተኮትኩቶ የማደጉ ጉዳይ ዘመናትን ተሻግሮ የመጣ ነው። ወደፊትም መቀጠል ያለበት ነው።

ዛሬ ሕፃናት በተለይም የእጅ ስልኮች ተጠቃሚ መሆን በመጀመራቸው ድሮ ከምናውቀው ከዚያ የአስተዳደግ ሥርዓት እና ከማህበራዊ አውዱ በመጠኑም ቢሆን አፈንግጠው የሚያድጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የእጅ ስልክ መያዙም ይሁን ሌላ ቴክኖሎጂን መጠቀሙ ዘመናቸው ለእነርሱ ያበረከተላቸው አንዱ እድል ሊሆን ይችላል፤ እርግጥ ነው ልጆችን ከተቀረው ዓለም ጋር አብረው እንዲራመዱና ለነገሮች አዲስ እንዳይሆኑ ከቴክኖሎጂዎች ጋር ማላመዱ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም። ዋናው ጉዳይ ግን ያገኙትን የቴክኖሎጂ እድል በወጉ ወይም በኃላፊነት የሚጠቀሙ ስለመሆናቸው ምን ያህል እርግጠኞች ነን? የሚለው ነው።

ባለንበት ዘመን አብዛኛዎቹ ታዳጊዎች የእጅ ስልኮች ላይ አቀርቅረው ማሳለፍን ስለሚወዱ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ተግባቦት ቀንሰዋል። በዚህም ስለሀገራቸውና ስለባህላቸው ከአያቶቻቸው፣ ከወላጆቻቸውና ከታላላቆቻቸው የሚያገኟቸውን ጠቃሚ ምክሮች አጥተዋል። በምትኩ በማህበራዊ ሚዲያ የሚተላለፉ እና እነርሱን የማይመጥኑ ጸያፍ አባባሎችን እያዳመጡና ምስሎችን እያዩ ከሀገራቸው እሴቶች ላፈነገጡ መጥፎ አስተሳሰቦችና ባህሪዎች ተጋላጭ ሆነዋል።

ያለንበት ዘመን ዓለም ወደ አንድ መንደር የተሰባሰበችበት ነው። ለዚህም ትልቁን ሚና የተጫወተው የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው። ዛሬ በግለሰብ ደረጃ ከአንዱ የዓለም ጠርዝ ወደ ሌላው የዓለም ጠርዝ በማይክሮ ሰከንድ ውስጥ የድምጽና የምስል መረጃ ተደራሽ መሆን ይችላል። እንደፌስ ቡክ ፣ቴሌግራም፣ ቲዩተር፣ ዩቲዩብ፣ ቲክቶክ፣ የመሳሰሉትና ሌሎቹም የማህበራዊ ሚዲያ መተግበሪያዎች ይህን ሚና ለመወጣት ጥቅም ላይ ውለዋል።

በእነዚህ መተግበሪያዎች አማካኝነት በርካታ ቁም ነገሮች መተላለፋቸውን አንክድም። አስተማሪና አዝናኝ መረጃዎች ተደራሽ ሆነዋል፤ አዳዲስ ግኝቶች ተዋውቀዋል፣ ችግረኞች ተጎብኝተዋል፤ ግብይቶች ተፈጽመዋል፤ በአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሳይንሳዊ ሁነቶች ተንሸራሽረዋል፤ በዚህ ሂደትም የሰዎች የመፍጠር አቅም አድጓል።

ማህበራዊ ሚዲያዎች እንደተባለውም ዓለምን ወደ አንድ መንደር ያሰባሰቡ ናቸው፤ የአንዱን ሀገር ባህልና አሠራር ለሌላው ሀገር የማስተዋወቅ ሚናቸውም የጎላ ነው። ይሁንና የአንዱ ሀገር ባህል ከሌላው ሀገር ባህል ጋር ሊጋጭ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። አንዳንድ ቁጥጥር የማይደረግባቸውና ልቅ ሆነው ትውልድን ልቅ የሚያደርጉ ማህበራዊ ሚዲያዎች ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በላይ በትውልድ ሥነ-ምግባር ቀረጻ ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ የከፋ ሊሆን ይችላል።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ያሉና የራሳቸው ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴት ያላቸውን ሀገራት ማህበራዊ መዋቅር ከመጉዳትና ከማፍረስ አንጻር አሉታዊ ግጽታ አላቸው። በተለይም ሕፃናት በሀገር በቀል ወግና ሥርዓት ተገርተው እንዳያድጉ፤ ከሀገራቸው እሴት ያፈነገጡ አስተምህሮዎችን እንዲከተሉ ተጽዕኖ ሊያሳድሩባቸው ይችላሉና ነው። ይህ ደግሞ በተግባርም ጭምር የታየ ነው። ልጆች ከመስማትና ከማየትም አልፈው አጫጭር የቪዲዮ ክሊፖችን እየሠሩ ሲለጥፉም ጭምር ታይቷል።

የሰብስክራይበርስን ቁጥር ለማብዛት ሲሉም ከኢትዮጵያዊ ወግና ባህል ያፈነገጡ ጸያፍ ንግግሮችንና ድርጊቶችን ሳይቀር በማህበራዊ ሚዲያ ሲያስተላልፉ ተመልክተናል። ወላጆች ልጆቻቸው የሚጠቀሙትን የማህበራዊ ሚዲያ አይነትም ሊመርጡላቸውና በተገቢው መንገድ እንዲጠቀሙ አቅጣጫ ሊያመላክቷቸው ግድ ይላል።

‹‹ወፍ እንደ ሀገሯ ትጮሃለች›› ይባላልና ከውጪ ዓለም የምናገኛቸውን አዳዲስ እውቀቶች ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማጣጣም ግድ ይለናል። ሕፃናት ተንቀሳቃሽ ስልክ በእጃቸው አስገብተው በባእዳን አስተሳሰብና ባህል ከመጠለፋቸው በፊት የራሳቸውን እሴት አውቀው እንዲያድጉ ማድረግ ያስፈልጋል።

ወላጆች ልጆቻቸውን በኢትዮጵያውያን እሴትና በጥሩ ሥነ-ምግባር ኮትኩቶ የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው። ልጆቻቸው ማገናዘብ በማይችሉበት የእድሜ ክልል ላይ እያሉ የእጅ ስልክ ገዝቶ ከመስጠት ሊቆጠቡ ይገባል፤ ስልክ መስጠት ግድ ሆኖ ከተገኘም መጠቀም ያለባቸውን እና መጠቀም የሌለባቸውን ነገር ማሳወቅ እንዲሁም አጠቃቀማቸውን መከታተልና መቆጣጠር ከወላጆች ይጠበቃል።

በአሁኑ ሰዓት አሜሪካንን ጨምሮ አንዳንድ ሀገራት የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም በሕፃናት ላይ እያሳደረ ያለውን ተጽዕኖ እየገመገሙ ይገኛሉ፤ በተለይም ‹‹ቲክቶክ›› ላይ ማእቀብ እስከ ማድረግ የደረሱ ሀገራት እንዳሉ ሲዘገብ ሰምተናል። በሀገራችንም የሕፃናትና የማህበራዊ ሚዲያ ቁርኝት ልጓም ሊበጅለት ይገባል።

በተለይም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ ጉዳይ እልባት ሊሰጥ ይገባል፤ ወላጆች ልጆቻቸው የማህበራዊ ሚዲያ ሱሰኛ ሆነው ከኢትዮጵያዊ ወግ ልማዳቸውና ባህላቸው እንዳያፈነግጡና መልካም ሥነ-ምግባር ተላብሰው እንዲያድጉ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል እንላለን።

## ነፃ ሃሳብ

# የመመሪያው ፋይዳ፣ስጋትና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

**ታምራት ተስፋዬ**

ሀገራት ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ብልፅግናን ለመቋደስ የአንድነትን ኃይል፣ የሕብረትንም የድል ምስጢር ጠንቅቀው በመረዳት በተለይ በንግድና ኢንቨስትመንት እርስ በእርስ መተሳሰርን አማራጭ ማድረግ ከጀመሩ ዓመታትን አስቆጥረዋል።

**ዓለም አቀፉ ምስል**

ከመገፋፋት ይልቅ መደጋገፍ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ራስ ወዳድ እና ስግብግብነትን በማስወገድ እርስ በእርስ ያላቸውን መስተጋብር ለማጠናከር እንዲሁም በኢኮኖሚ አቅም በእኩል ደረጃ መወዳደርም ሆነ መደራደር የሚያስችላትን አቅም ለማጎልበት በአሁን ወቅትም የተለያዩ ተግባራት በማከናወን ላይ ተጠምደዋል።

በኢኮኖሚ ልዕልና ስማቸው አንቱ የሚባልላቸውን ጨምሮ በርካታ ሀገራትም በዚሁ መንፈስ እየተመሩ መጪውን ለማሳመር በመትጋት ላይ ይገኛሉ። በተለይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ልዩ ትኩረት ሰጥተው፣ የተለያዩ ተግባራትን በመከወን ላይ ናቸው።

የምጣኔ ሀብት ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ አንድን ሀገር ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ተፈላጊና ሳቢ የሚያደርጋት የዘረጋችው ሀገራዊ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ነው። ይሁንና ምቹ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፍ መኖሩ ብቻ ፍሰቱን እንዲጨምር ላያደርግ ይችላል። ሀገራት በተለይ ውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመትን ለመሳብ በየጊዜው አሉኝ የሚላቸውን አማራጮች ብሎም ምቹ ሁኔታዎችን ማስተዋወቅ የግድ ይላቸዋል።

በአሁን ወቅትም በዓለም አቀፍ ደረጃ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና ለመሳብ የሚያደርግ ፉክክሩ ይበልጥ እያጦዘ መጥቷል። ይህ እንደመሆኑም ሀገራት የተቀናጀ ጠንካራ ሥራ መሥራትና ሁሉ አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማጠናከር ግድ ብሏቸዋል።

ኢንቨስተሮችም በአንድ ሀገር መዋዕለ ነዋያቸውን ፈሰስ ከማድረጋቸው አስቀድሞ ውጤታማ መሆን የሚያስችላቸውን በርካታ መመዘኛዎች ያስቀምጣሉ። መዋዕለ ነዋያቸው ፈሰስ ለማድረግ ሲያስቡም የገበያ አዋጭነት፣ የደንበኞች ቁጥር፣ የግብዓት እንዲሁም የመሠረተ ልማት አቅርቦትን እና ተደራሽነት መጠንን ይቃኛሉ። የቢዝነስ አመቺነት ‹‹Ease of Doing Business››ን ጨምሮ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ነክ ተቋማት የሚወጡ መረጃዎችንም ያማትራሉ።

**የኢትዮጵያ መልክ**

ኢትዮጵያ ከአንድ መቶ አስር ሚሊየን በላይ ሕዝብ ያላት ሀገር ናት። ይህ ቁጥር በገበያ መነፅር ሲታይ ከፍተኛ አቅምና ፍላጎት እንዳለ ማረጋገጫን የሚሰጥ ነው። ከሰው ኃይል ባሻገር ሀገሪቱ በዓይነት ብዙ የተፈጥሮ ሀብት የተንቆጠቆጠች መሆኗም ለኢንቨስትመንት ገበያ ምቹ እንድትሆን ከፍተኛ አቅም ከሚፈጥሩት መካከል የሚጠቀስ ነው።

ይሁንና ኢትዮጵያ ቢዝነስ አመቺነት ስትቃኝ መሻሻሎችን ብታሳይም መሆን ከሚገባት ደረጃ ላይ እንዳልሆነች የሚካድ አይደለም። የተለያዩ የምጣኔ ሀብት ምሁራንም፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ከትርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ከሁሉ በላይ የተቋማት አቅም መጎልበት በተለይ ሕግ እና ሥርዓትን በአግባቡ መተግበር የግድ ነው ይላሉ። በተለይ የውጭ ኢንቨስመንትን ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ ኢንቨስተሮች ጉዳያቸው በቀላሉ ማስፈፀም እንዲችሉ የማድረግ ተግባር ጠንካራ የድጋፍና የክትትል አሠራርን እንዲሁም ቅንጅትን እንደሚጠይቅ አፅእኖት ይሰጡታል።

ይህ ተግባር እንደ ኢትዮጵያ ባሉ መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ከወረዳ ጀምሮ እስከ ከተማና ክልል እንዲሁም ፌዴራል ደረጃ የሚዘልቅ ነው። ይሁንና በሀገሪቱ ይህን ሥራ በተሻለ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ መናገር የሚቻለው በፌዴራል ደረጃ ብቻ ነው። ኢንቨስተሮቹ ወደ ክልልና ዞን ብሎም ቀበሌ ሲወርዱ የሚገጥማቸው በፌዴራል ደረጃ ከሚያገኙት የተቃረነ ነው። ችግሩም ለኢንቨስተሮቹ ምሬት እና ተስፋ መቆረጥ በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ሁነኛ ማነቆ ሆኖም ቆይቷል።

**ለውጦች**

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስተዳደር ወደ ስልጣን ከመጣ ጊዜ አንስቶም፣ ይህን መልክ ለመቀየርና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ ለማበረታታት፣ ለማስተዳደርና ለመጠበቅ የሚያስችል አመቺ ከባቢ ሁኔታን ለመፍጠር አዳዲስ ተከታታይ የሪፎርም ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

ቀደም ባሉት ዓመታት የወጡና የዘርፉን እድገት የሚገዳደሩ አንዳንድ ሕጎችና ደንቦች እንዲወገዱም ተደርጓል። የኢንቨስትመንት ፖሊሲን ስር ነቀል በሆነ መልኩ በማጎልበት በየጊዜው ከታዩ ልምዶች ትምህርት በመውሰድ፣ ለውስጥም ሆነ ለውጭ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎች ለመፍጠር የተለያዩ ርምጃዎች በመውሰድ ላይ ናቸው።

በተለይም ተጨማሪ ሀብት፤ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ መፍጠርና ማጎልበትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ባለፉት ስድስት ዓመታት በመንግሥት ተይዘው የነበሩ ዘርፎችን ሙሉ በሙሉና በከፊል ወደ ግሉ ዘርፍ የማዞር ብሎም ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት ለማድረግ ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን የሚታወስ ነው። ከውጭ ባለሀብቶች ባሻገር የግል ዘርፉን በተለይ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ለማበረታታትና ሁለንተናዊ አቅማቸውን በማሳደግ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚወረወሩትን ጠጠር ለማብዛትም ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል።

መንግሥት ከዚህ ጎን ለጎን የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ፍትሐዊ ያልሆነ ውድድር እንዳይገጥማቸው፣ በጥራትና በብዛት የመሥራት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ገበያ የእሴት ሰንሰለት የመዋሃድ አቅማቸውን በማሳደግ፣ በሂደትም እሴት የታከሉባቸው ኢንቨስትመንቶችን መፍጠር እንዲችሉ በሚል የተወሰኑ የንግድ ዘርፎችን ከውጭ ሀገሮች ኢንቨስተሮች ተሳትፎ ከልሎ መቆየቱም የሚዘነጋ አይደለም።

መንግሥት በተለይም የሀገር ውስጥ ነጋዴዎችን ለመጠበቅ በጅምላና ችርቻሮ ንግድ ላይ የውጭ ባለሀብቶች እንዳይገቡ ሲከላከል ቆይቷል። ይህም ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከለላ ሲሰጥ ራሳቸውን ጠቅመው ሀገርንም ይደግፋሉ በሚልና የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ ማድረግን ታሳቢ በማድረግ ነው።

ይሁንና ይህ ከለላ የሚፈለገው ለውጥ ማምጣት አልሆነለትም። ይህን ተከትሎም አማራጭ ማፈላለግ ግድ ሆኖበታል። ካለው የሀገሪቱ ፍላጎት አንፃር የግብይት ሥርዓቱ በተጨማሪ ተዋንያኖች ካልታገዘ የሚያስከትለው ጉዳት ቀላል እንዳልሆነ ግንዛቤ ተወስዷል። ከሰሞኑም እስካሁን ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ተለይተውና ተጠብቀው በቆዩ የንግድ ዘርፎች ላይ ማሻሻያ መደረጉ ተገልጿል።

ባሳለፍነው ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም የኢንቨስትመንት ኮሚሽንና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፣ የውጭ ኢንቨስተሮች ከዚህ ቀደም ተከልክለው በነበሩ ማለትም የወጪና የገቢ ንግድ፣ እንዲሁም የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ውስጥ እንዲሳተፉ የሚፈቅድ መመሪያ በኢንቨስትመንት ቦርድ መፅደቁን ገልጸዋል። በመመሪያው ውስጥ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟሉ የውጭ ባለሀብቶች ፈቃድ እንደሚሰጣቸው ተመላክቷል።

**ፋይዳው**

ለኢትዮጵያውያን ብቻ ይፈቀዱ የነበሩ የንግድ ሥራዎች ለውጭ ኩባንያዎች ቀስ በቀስ እየተከፈቱ ስለመሆናቸው አንድ ማሳያ ተደርጎ የተወሰደው ይህ ማሻሻያ፣በኢትዮጵያ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ተጨባጭ ለውጥ እንደሚያመጣም ታምኖበታል።

ሕጉ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ተከልሎ የነበረውን የጅምላና ችርቻሮ የንግድ ሥራ ለውጭ ኩባንያዎች በመፍቀድ ብቻ የተገደበ ሳይሆን በወጪና ገቢ ንግድ ላይም የውጭ ባለሀብቶች ተሳታፊ የሚሆኑበትን በር የሚከፍት በመሆኑ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ አዲስ አሠራር እንደሚፈጥርም አያከራክርም።

በዘርፉ የውጭ ኩባንያዎች ከገቡ ቢዝነሱ በተወዳዳሪነት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት የሚሰጥበት እንደሚሆን አያጠርጥርም። ይህ ደግሞ በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ የግሉ ዘርፍ ልምድም እንዲቀሰምበት እንዲያድግ ምክንያት ይሆናል። ከውድድር በተጨማሪ ቴክኖሎጂ፣ እውቀትና አዳዲስ አሠራሮችን ያስተዋውቃል።

ማሻሻያው በጥቂቶች የተያዘውን የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ሥራ ተወዳዳሪ እንዲሆን በማድረግ ገበያን ማረጋጋት የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ነው። በተለይም ንግዱ ዘርፍ የሚታዩ ሕገ ወጥ አሠራሮችን ለማሻሻልና ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓት ለመዘርጋት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በተለይ ሕጋዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን በማድረግ ለዋጋ መረጋጋት ከፍተኛ አቅም ለመፍጠር አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ከሸማቹ ወገን ፋይዳቸው ጉልህ ነው።

የኮንትሮባንድ ንግድን በማስቀረት በሕጋዊ መንገድ የሚደረግ የንግድ እንቅስቃሴን የማሳደግ አቅሙም ግዙፍ ነው። የግብይት ሥርዓቱን መስመር ከማስያዝ ባሻገር የመንግሥትም የግብር ገቢ በማሳደግ ረገድ ያለው ፋይዳም እጅጉን ከፍተኛ የሚባል ነው።

የሀገሪቱ የግብይት ሥርዓትን ለማስተካከል ከመርዳቱም በላይ ሀገሪቱ በወጪ ንግድ ዘርፍ ያላትን ተወዳዳሪነት ይጨምራል። ማሻሻያው በተለይ ሀገሪቱ ለዓመታት የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት የምታደርገውን ጉዞ ለማሳለጥ፣ የሚኖረው አስተዋፅኦም በቀላሉ ሊታይ አይገባም።

የማሻሻያው አጠቃላይ ድምር ውጤትም የኢትዮጵያን ኢንቨስትመንትና ኢንቨስተሮች ለማጎልበትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አቅም የሚፈጥሩ ናቸው። በተለይም አዳዲስ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚደርገውን ጥረት በማገዝ ረገድ ሚናቸው የጎላ ነው።

**ስጋቶች**

ይሁንና ማሻሻያው መሰል ትሩፋቶች እንዳሉት የውጭ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ መግባታቸው በሀገር ውስጥ ተመሳሳይ ሥራ በሚሠሩ ነጋዴዎች ላይ ጫና ይፈጥራል። የውጭ ኢንቨስተሮች የውጭ ምንዛሪ የማቅረብ አቅማቸው ከፍተኛ ስለሆነ ብዙ የውጭ ምንዛሪ ይዘው ስለሚመጡ የሀገሬው ነጋዴ ሊወጣ ይችላል የሚል ስጋት ያላቸውና መከራከሪያ የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ። የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ተወዳዳሪ አቅም እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑም ለጭንቀታቸው ዋነኛ ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ። የጥቁር ገበያ ችግርም ሌላኛው ራስ ምታት መሆኑን ያነሳሉ።

በርግጥም መሰል ስጋቶች ተገቢ ናቸው። ይሁንና ኢትዮጵያ በየትኛውም መስፈርት ከዓለም የግብይት ሥርዓት ውጪ ልትሆን አትችልም። ሁለንተናዊ አቅምን ለማጎልበት መዘጋጀት እንጂ ስጋትን ታሳቢ በማድረግ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ራሳችንን አልቻሉምና ሊመጡ አይገባም ማለት ከዚህ በኋላ ብዙ ርቀት የሚያስኬድ አይደለም።

እስካሁን በመጠበቅ የተከፈለው ዋጋም ለዚህ ምስክር መሆን የሚችል ነው። ይህ እንደመሆኑም አሁን ላይ መፍትሔው ከፍ ላለ ውድድር ራሳቸውን ማዘጋጀት ብቻ ነው። ከዚህ ባለፈ እንዴት ባለ መልኩ በጥምረት /በጆይንት ቬንቸር /መሥራት እንደሚችሉ መዘየድን ሊዘነጉ አይገባም።

**ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮችና ቀጣይ ሥራዎች**

መንግሥት በየደረጃው ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት እየወሰዳቸው ያሉ ወሳኝ የሆኑ ሥራዎች ትርጉም ያለው ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉት የተለያዩ አካላት የተቀናጀ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደመሆኑ በዚህ ረገድ ሰፊ ሥራዎችን መሥራት የግድ ይላል።

ኢንቨስተሮቹ ከመጡ በኋላ እንዴት ውጤታማ በሆነ መልኩ መስተናገድ አለባቸው፣ በሥራ ሂደት የሚያግጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እንዴት ፈጣን በሆነ መልኩ መፍታት ይቻላል የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ሥራ መሥራትም ይገባል። ይህን የሚከታተሉ ባለሙያዎችን አቅም በየጊዜው ማጎልበት ተገቢ ነው።

በትግበራ ወቅት ከቁጥጥር ጋር በተያያዘ በሚስተዋሉ ድክመቶችና በሚፈፀሙ ሕገ ወጥ ተግባራት ሀገር የሚያስፈልጋትና ወደ ሀገር የሚገባው የተለያየ ሊሆን ይችላል። የዘርፉ ተዋናዮች እንጂ ሀገር የምትፈልገው ላይገባም የሚችልበት እድል ይኖራል። አሠራሩ ጥንቃቄ ካልተደረገበት ግለሰቦች በትይዩ ገበያ ገዝተው ያስቀመጡትን ወይም ያጠራቀሙትን የውጭ ምንዛሪ የሚያጠቡበት ወይም ሕጋዊ የሚያደርጉበት ሁኔታን ሊያመቻች ይችላል።

> **በተለይም ሕግና ደንቦችን ተከታትሎ የማስፈጸም አቅሙ ደካማ ከሆነ ማሻሻያው አደገኛ መሣሪያ የመሆን ዕድል እንደሚኖረው እሙን ነው። ይህ እንደመሆኑም በአስገዳጅነት የተቀመጡ ድንጋጌዎችንና አሠራሮችን በአግባቡ ስለማካሄዳቸው መቆጣጠር የግድ ይላል**

በተለይም ሕግና ደንቦችን ተከታትሎ የማስፈጸም አቅሙ ደካማ ከሆነ ማሻሻያው አደገኛ መሣሪያ የመሆን ዕድል እንደሚኖረው እሙን ነው። ይህ እንደመሆኑም በአስገዳጅነት የተቀመጡ ድንጋጌዎችንና አሠራሮችን በአግባቡ ስለማካሄዳቸው መቆጣጠር የግድ ይላል።

በአጠቃላይ ማሻሻያው ያላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል መጠንቀቅ ያስፈልጋል። የማሻሻያውን ዓላማ ለማሳካት ሳይሆን የራሳቸውን ጥቅም ለማዳበር የሚፈልጉ ግለሰቦች ያላግባብ እንዳይጠቀሙበት ሂደቱ በጥብቅ ሥነ ምግባር ሊመራ ይገባል።

በማሻሻያ ውጤት ታይቷል? ገበያውስ ተረጋግቷል? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ በየጊዜው መቃኘት መዘንጋት አይኖርበትም። አፈፃፀሙን በየጊዜው በመከታተል የተፈለገውን ውጤት አምጥቷል፣ አላመጣም፣ ችግሮችና መፍትሔዎቹስ የሚለውን መገምገም ያስፈልጋል። ከዚህም ከፍ ሲል ውጤቱ እየታየ ማሻሻያዎች ካስፈለገ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል።

ሌላው ልዩ ትኩረት እና መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባ ሀገሪቱ ውስጥ ስር ሰዶ የሚገኘው ግዙፍ የሙስና ወንጀል መከላከል ማስቆም መሆኑም የሚያከራክር አይደለም። ሙስናን መቆጣጠር አለመቻል ገበያውም ጤናማ አየር እንዳይተነፍስ በማድረግ በኢንቨስመንት ፍሰት እና በኢንቨስተሮች ሥነ ልቦና ላይ ከባድ ጫናን ይፈጥራል። ይህ እንደመሆኑም ማሻሻያው የተፈለገውን ግብ እንዲመጣ ሕገ ወጥ ተግባሩን የእውነት መታገል ያስፈልጋል።

በተለይም ከሰላም እና ጸጥታ ጋር ተያይዞ የሚነሱት ችግሮች ፈጣን እልባት መስጠት፣ ሎጂስቲክስና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ በቋሚነት የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግና ከውስጥ ፍላጎት አልፎም የውጭ ምንዛሬ ማስገባት የሚያስችሉ ዋና ዋና ምርቶችን በስፋት በሀገር ውስጥ ማምረት ብሎም ለውጭ ገበያ ማቅረብ ታሳቢ አድርጎ ዘወትር መሥራት ይገባል። በተለይ የፍላጎትና አቅርቦት ምጥን ልዩነቱን ለማስተካከል ሀገር ውስጥ በተሻለ ማምረት የሚችልበትን መንገድ መቀየስና ለዚህ ተግባራዊነትም ሌት ተቀን መትጋት የግድ ይላል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## በዲጂታል መታወቂያ ተደራሽነት/ የኢትዮ ቴሌኮም ዝግጁነት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በ2025 የዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂን እውን ለማድረግ በርካታ ተግባራት እያከናወነች ትገኛለች። ስትራቴጂውን እውን እንዲሆን ከሚያደርጉ አስቻይ ሁኔታዎች መካከል ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ አንዱ ነው። መታወቂያው አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይታመናል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ዲጂታል መታወቂያ ከዜጎች በሚወሰዱ ውስን የባዮሜትሪክስ እና ዲሞግራፊክ መለያዎች አማካኝነት የተረጋገጠ መረጃ ለማቅረብ የሚያስችል ሲሆን፤ የዲጂታል ሥነ ምህዳር ለመፍጠር የላቀ ሀገራዊ ፋይዳ አለው። ለአካታች የማህበራዊ ኢኮኖሚ እድገት፣ ለቢዝነስ ትስስር፣ ለኢ-ጋቨርንመንት አገልግሎት፣ በዳታ የሚመራ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት፣ ለቀልጣፋ ማህበራዊ አገልግሎት፣ ለተሻለ የዜጎች ሕይወት እና የሳይበር ማጭበርበርን ለመከላከል አስተማማኝ ወሳኝ መሆኑ ይገለጻል።

አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን ለዜጎች ለማቅረብ፣ የላቀ የደንበኞች አገልግሎት ተሞክሮን እውን ለማድረግ፣ የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት፣ የኢኮሜርስ ግብይትን ለማሳለጥ፣ የፋይናንስ አካታችነትን የሚጨምሩ የአነስተኛ ብድር አገልግሎቶችን ያለ ዋስትና ለማቅረብ፣ የክሬዲት ግብይት ለማስፋፋት፣ የብድር ምጣኔን ለማሻሻል እንዲሁም የዜጎችን የአኗኗር ዘይቤ የሚያዘምኑ እና ቢዝነስን የሚያቀላጥፉ የዲጂታል አገልግሎቶችን ለማቅረብ ያስችላል። በሀገሪቱ የተማከለ ብሔራዊ የዲጂታል መታወቂያ ዳታቤዝ ለመገንባት ለቢዝነስ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈጣን እና አስተማማኝ የማንነት ማረጋገጫ በመስጠት የተሻለ አሠራርን እንዲተገብሩ ይጠቅማል።

ይህ ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆን ለማስቻል በብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት አማካኝነት ብዙ እየተሠራ ነው። በቅርቡም በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ዲጂታል መታወቂያ ተደራሽ እንዲሆን እና ሁሉም ዜጋ በፍጥነት አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ኢትዮ ቴሌኮም ከብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት ጋራ ለመሥራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ፈርሟል።

በስምምነቱ ወቅትም ኢትዮ ቴሌኮም በሀገር አቀፍ ደረጃ በ29 ከተሞች የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ምዝገባን አስጀምሯል። በኩባንያው 32 ሚሊዮን ዜጎችን የዲጂታል ተደራሽ በማድረግ ሀገራዊ እቅዱን 36 በመቶ ያህል ለማሳካት አቅዶ ሥራ ጀምሯል።

ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ አስቻይ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ተዓማኒነት ያለው የማንነት መለያ ዲጂታል መታወቂያ መሆኑን የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍሬሀይወት ታምሩ አስታውቀዋል። ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባትና ዜጎች በኢኮኖሚው እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ይፈጥራል ሲሉ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የዲጂታል እድሎችን መጠቀም ፈጠራ የታከለበትና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ለመገንባት ወሳኝ ነው። ኢትዮ ቴሌኮም ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን እውን ለማድረግ በርካታ መሠረተ ልማቶች እየገነባ ይገኛል። ስትራቴጂውም አራት ዋና ዋና አስቻይ ሚና ይጫወታሉ ተብለው የተለዩ ጉዳዮች አሉት። የመጀመሪያው ኮኔክቲቪቲ (የሞባይል የኢንተርኔት እና የመሳሳሉት) ሲሆን፤ አገልግሎቶችን በሰፊው ተደራሽ ማድረግን ይመለከታል። ሁለተኛው አስቻይ ሁኔታዎችን /ኢነበሊንግ ሲስተም/ ሲሆን፣ አስቻይ ሲስተሞች ከሚባሉት መካከልም አንደኛው ዲጂታል መታወቂያ ነው።

ዲጂታል መታወቂያ ዜጎች በየትኛውም ስፍራ፣ በማንኛውም ሰዓት ማንነታቸውን የሚገልጽ ተዓማኒነት ያለው መለያ እንዲኖራቸው ያስችላል። ይህ ሲሆን ደግሞ በመንግሥትና በዜጎች መካከል በቀላሉ መረጃ መለዋወጥ ብቻ ሳይሆን፣ የአገልግሎት ተደራሽነት የሚረጋገጥበት እድል ይፈጠራል። ይህም አስቻይ ሁኔታ ዲጂታል መታወቂያን ብቻ ሳይሆን እንደ ቴሌብር ያሉ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶችንም ይዟል።

ሦስተኛው ምህዳሩን ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ ነው። ይህም በቀላሉ የመንግሥት አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ ዜጎች ካሉበት ሆነው በተቀላጠፈና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ አገልግሎትን እንዲያገኙ ያስችላል። አገልግሎቶችን በፍጥነት ተደራሽ ለማድረግ እድል ይፈጥራል።

አራተኛውና የመጨረሻው ምህዳሩ /ኢኮ ሲስተም/ እንዲኖር ያስፈልጋል። የዲጂታል ምህዳሩ የሚፈልገውን እውቀት ለማምጣት ሰዎች ላይ መሥራት ይጠይቃል። ምቹ የሆኑ አስቻይ የፖሊሲና ሪጉሌሽን ሥርዓቶችን መዘርጋትንም እንዲሁ ይጠይቃል።



**በሀገር ደረጃ 2018 ዓ.ም 90 ሚሊዮን ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ እንዲያገኙ ታቅዷል። ይህን እቅድ ለማሳካትም ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፤ በወር በአማካኝ አንድ ሚሊዮን ዜጎችን ለመመዝገብ ታቅዷል። ከ90 ሚሊዮን ዜጎች ውስጥ ኢትዮ ቴሌኮም 32 ሚሊዮን የሚሆኑትን ለመመዝገብ አቅዷል**

ዲጂታል መታወቂያ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን በማድረግ ረገድ በርካታ አስቻይ ሁኔታዎች መፍጠር ይችላል የሚሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ከዲጂታል ኢትዮጵያና ከዲጂታል ኢኮኖሚ አንጻር ሲታይ አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመፍጠር ትልቅ እድል እንደሚፈጥር አስታውቀዋል። ዲጂታል ኢኮኖሚ እየገነባን ተደራሽና አካታች ካልሆነ ትርጉም አልባ ይሆናል ሲሉ ያስረዳሉ።

ዲጂታል መታወቂያ ለአካታች ኢኮኖሚ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሁሌም ዜጎች በኢኮኖሚ ግንባታ የሚሳተፉበት እድል የሚፈጠርበትና ከዲጂታል ኢኮኖሚ የሚገኙ ቱሩፋቶችን ተጠቃሚ መሆን የሚችልበትም እንደሚሆን አመልክተዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ሀገራት ለዜጎቻቸው ተአማኒነት ያለው መለያ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። ዜጎች በየትኛውም ቦታ ሆነው ማንነታቸውን ማረጋገጥ የሚችሉበት ተአማኒነት እና እውቅና ያለው መለያ ሊኖራቸው ይገባል። አንድ ዜጋ ይህ ዲጂታል መታወቂያ ሲኖረው ደግሞ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ራሱን ማሳተፍ እንዲችል ትልቅ እድል ይፈጥርለታል። የሕዝብና የመንግሥት አገልግሎት የሚባሉትን በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ ያስችላል።

ለአብነት ለዜጎች የጤና እንክብካቤ ለመስጠት ሲፈለግ በዲጂታል መታወቂያ ማንነቱን በማረጋገጥ ካለበት ስፍራ ሆኖ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ ይቻላል። በአገልግሎት ሰጪውም ሆነ በተቀባዩ መካከል ተአማኒነት ይፈጥራል። ይህ ሲሆን ደግሞ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትን ለማሳለጥ፣ ኢ ኮሜርስና አዳዲስ አገልግሎቶች ተደራሽ ለማድረግ መደላደል ይፈጥራል። አካታች የሆነ አስተዳደር እንዲኖር ስለሚያደርግ ዜጎች ካሉበት ሆነው መደበኛ የሚባሉ የመንግሥት እና ሌሎች አገልግሎቶች በእኩል ማግኘት የሚችሉበትን እድል ለመፍጠር ያስችላል።

“ዲጂታል መታወቂያ በመረጃ የሚመራ ኢኮኖሚን ለመገንባት ያስችላል፤ እንዲህ ዓይነት ኢኮኖሚ ስንገነባ ደግሞ በመረጃ ላይ የተመሠረተ የፖሊሲ ማሻሻያ ለማድረግ እንችላለን» የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ኢኮኖሚውን ለመገንባትም ሆነ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት መረጃ ላይ የተመረኮዘ ማሻሻያ እንዲደረግ በእጅጉ እድል ይፈጥርልናል ይላሉ።

በዲጂታል ዓለም ሊከሰቱ የሚችሉ የተለያዩ ወንጀሎች ለመከላከል ያግዛል። የዲጂታል መታወቂያ መኖር ጊዜና ወጪ በመቆጠብ ዜጎችንም ሆነ አገልግሎት ሰጪዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፣ ዲጂታል መታወቂያ እንዲኖር የሚያስችል መሠረተ ልማት መገንባት የሚያስፈልገው በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች መሆኑን አብራርተዋል።

ብዙ ጊዜ ገንዘብና ጊዜ የሚባክነው ማንነትን ለማወቅና ለማጣራት በሚደረግ ሂደት እንደሆነ ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ጠቅሰው፤ ለዚህም ዜጎች በጣም ቀላል የሚባሉ አገልግሎቶችን ባሉበት ሆነው ማግኘት መቻላቸውን በአካል ቀርቦ እስከሚረጋገጥ ድረስ ረጅም ጊዜ ይፈጃል። ዲጂታል መታወቂያ መኖሩ ግን ለሰው ልጅ ዘመናዊ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ እንዲኖር እድል ይፈጥራል፤ ጊዜና ገንዘብንም ይቆጥባል ሲሉ አብራርተዋል።

የዲጂታል መታወቂያ መኖር ዜጎች ካሉበት ቦታ ሆነው ራሳቸውን በመግለጽ በቀላሉ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያስችል ጠቅሰው ፤ የንግድ ተቋማት ያላቸውም አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን ለገበያ ማቅረብ እንደሚያስችላቸው አመላክተዋል፡

ዲጂታል መታወቂያ ተግባራዊ ያደረጉ ሀገራት ኢኮኖሚያቸውን በማሳደግ ዜጎችና መንግሥት ያላቸውን ግንኙነት በማሻሻል አገልግሎቶች እንዲፋጠኑ ትልቅ እድል ፈጥሮላቸዋል የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በእኛ ሀገር ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በፍጥነት ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ባለፉት ጊዜያት እንደ ሀገር በተሠሩ ሥራዎች አራት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸው የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ካለው ሕዝብ ቁጥር አኳያ በዚህ አካሄድ ሁሉንም ተደራሽ ለማድረግ እንደማይቻል ተናግረዋል። ኢትዮ ቴሌኮም ይህን ክፍተት በመሙላት መታወቂያው በፍጥነት ተደራሽ እንዲሆን አልሞ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ እንዳብራሩት፤ ብሔራዊ የዲጅታል መታወቂያ ምዝገባው አዲስ አበባን ጨምሮ በ29 ከተሞች በይፋ የተጀመረ ሲሆን፣ ኢትዮ ቴሌኮም ዜጎች ተደራሽ ለመሆን በአገልግሎት መስጫ ማዕከላት አገልግሎቱን መስጠት ጀምሯል። በተጨማሪም ዜጎች ባሉበት ቦታ ሆነው በቴሌ ብር ሱፐርአፕ ምዝገባውን ማከናወን ይችላሉ። በቀጣይም ከአጋሮች ጋር በመሆን አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ በተለያዩ ከተሞች የማስፋፊያ ሥራ ይሰራል።

በሀገር ደረጃ 2018 ዓ.ም 90 ሚሊዮን ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ እንዲያገኙ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በወር በአማካኝ አንድ ሚሊዮን ዜጎችን ለመመዝገብ ታቅዷል ይላሉ። ከ90 ሚሊዮን ዜጎች ውስጥ ኢትዮ ቴሌኮም 32 ሚሊዮን የሚሆኑትን እንደሚመዘገብ አስታውቀዋል።

«ዲጂታል ኢኮኖሚው እየፈጠነ ዲጂታል መታወቂያ ወደኋላ የሚቀር ከሆነ ተደራሽ መሆን የሚቻለው ለጥቂቶች ብቻ ነው» የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ጤናማና ዘላቂነት ያለው፣ ሁሉም የዲጂታል ኢኮኖሚ ከሚያመጣው መልካም አጋጣሚ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት አሠራር መዘርጋት ወሳኝና አስፈላጊ ነው ብለው እንደሚያስቡ ተናግረዋል።

እሳቸው እንደተናገሩት፤ የብሔራዊ መታወቂያ አንደኛው ጠቀሜታ አካታችነት ማምጣት ስለሆነ ይህን ለማሳካት አንድ ሺ ሁለት መቶ የመመዝገቢያ ኪቶችን በመግዛት ሥራው ተጀምሯል። ይህን እቅድ ለማሳካት በአገልግሎት ማዕከሉ ብቻ ሳይሆን የሞባይል ቲም/ ቡድን/ እንዲኖር ይደረጋል። ሞባይል ቲም እንዲኖር ያስፈለገበት ምክንያት አንዳንድ ተቋማትና ስደተኞች ወደ አገልግሎት ማዕከላት መጥተው ለመመዝገብ ስለሚቸገሩ ነው፤ እነዚህ ወገኖች ባሉበት ሆነው ምዝገባውን ማከናወን እንዲችሉ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

በአዋጁ መሠረት ዲጂታል መታወቂያውን የማግኘት መብት ያላቸው ከአምስት ዓመትና ከአምስት ዓመት በላይ የሆኑ ዜጎች ሲሆኑ፤ ከኢትዮጵያውያን ውጭ ደግሞ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሕጋዊ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ያላቸው የውጭ ሀገር ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ እንዲወሰዱ ይፈቅዳል።

ዲጂታል መታወቂያውን ለመወሰድ የሚያስፈልገውን ማንነት የሚገልጽ የቀበሌ መታወቂያ፣ አልያም መንጃ ፈቃድ ያስፈልጋል፤ ከዚህ ውጭም የትኛውንም ዓይነት ሰነድ በመያዝ በአገልግሎት መስጫ በማቅረብ በፍጥነት አገልግሎት ማግኘት ይቻላል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከከተማ እና የገጠር ነዋሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲ፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና የብሔራዊ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተፈታኝ ተማሪዎች፣ በተፈናቃዮች ጣቢያ የሚገኙ፣ የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች እና ሕጋዊ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ያላቸው የውጭ ሀገር ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ ማከናወን ይችላሉ። ዲጂታል የክፍያ አገልግሎቶችን በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ወሳኝ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ሁሉም የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የውጭ ባለሀብቶች በጅምላና ችርቻሮ ንግድ መሳተፍ ፋይዳና ስጋት

**ምሕረት ሞገስ**



የንግድ ሥራ ማለት ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን ለዋጋ ሲባል መሸጥ፣ ማስተላለፍና መለወጥ ነው። ይህ ሁሌ የሚከናወን የግብይት ሂደት ሲሆን፤ ለትርፍ ሲባል የሚከናወን ነው። በዋናነት ደግሞ ርግጠኛነት የሌለው የመክሰርና የትርፋማነት ውጤት ሊያስከትል የሚችል ባህሪም እንዳለው በንግድ ሥራ ላይ የተካሔዱ ጥናቶች ያመለክታሉ።

የሀገሪቱን ንግድ ሕግና ሕገ-መንግሥት ስናይ፤ ንግድ የሰው ልጆች የዕለተ ተዕለት ኑሮን ለማሻሻልና ብሎም ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማራመድ የሚያስችል የኢኮኖሚ ግንኙነት እንደ መሆኑ መጠን ይህን የንግድ ግንኙነት በተፈለገው መንገድ ለማስኬድ የግድ በሕግ መገዛትን ይጠይቃል። ይህንን መሠረት በማድረግ በሀገራችንም በ1952 ዓ.ም የንግድ ሕግ ወጥቶ እንሆ ለግማሽ ምእተ ዓመት ገደማ እየተሠራበት ይገኛል።

በሕገ-መንግሥቱም አንቀፅ 43(1) ላይም "የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው። " በማለት የደነገገውን መሠረት በማድረግ የንግድና የኢንቨስትመንት ሥራው ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ተጠናክሮ እየተሠራበት ይገኛል።

በዚህ ሂደት የበለጠ ንግዱን ስኬታማ ለማድረግ እና ሸማቹን እንዲሁም ሀገርን በሚጠቅም መልኩ ለማካሔድ ከሚወጡ ደጋፊ ሕጎች መካከል ከሰሞኑ የችርቻሮም ሆነ የጅምላ ንግድ ላይ የውጭ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ የተፈቀደበት አዲሱ አዋጅ አንደኛው ነው።

በገቢ፣ በወጪ፣ በጅምላ እና በችርቻሮ ንግድ ላይ የውጪ ባለሀብቶች እንዲሠማሩ የሚፈቅድ ምንም ዓይነት የአሠራር ሥርዓትም ሆነ ደጋፊ ሕግ እና መመሪያ አልነበረም። ይህም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚፈለገው መጠን እንዳያድግ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር እንዲሁም የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከሰሞኑን የኢትዮጵያ የንግድ እንቅስቃሴ ለውጭ ባለሀብቶች መፈቀዱን አስመልክቶ መግለጫ በሰጡበት ወቅት አስታውቀዋል።

የፈቃዱ መሰጠት በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ላይ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚያስችል እና በተሻለ ውድድር ሸማቹ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገዛ ያደርጋል ብለዋል። በርግጥ በወጣው መመሪያ ለውጪ ባለሀብቶች ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳሉ ተብራርቷል።

አዲሱን የውጭ ባለሀብቶች የንግድ ፈቃድ አስመልክቶ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የሚሉት አላቸው። በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር እና ተመራማሪ ረዳት ፕሮፌሰር ፍሬዘር ጥላሁን እንደሚናገሩት፤ ለውጭ ባለሀብት ዝግ ተደርጎ የቆየው የግብይት ሥርዓትን መከፈቱ ትልቅ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ነው። ምክንያቱም በሀገር በቀል ባለሀብቶች ብቻ ተይዞ የነበረው፤ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ሲደረግ ተወዳዳሪነትን ለመጨመር እና ጥራትን እና የተሻለ አገልግሎት ሕዝቡ እንዲያገኝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ይህ ማለት የውጭ ነጋዴዎች ሲመጡ፤ ሀገር ውስጥ ያሉትም ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ እና አብሮ ለመልማት እንዲሁም ለጋራ ዕድገት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል ማለት መሆኑን ይናገራሉ። እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ፍሬዘር ገለፃ፤ የውጪዎቹ ሲመጡ እና ሲሳተፉ አዲስ የግብይት ሥርዓትን ያስለምዳሉ። ቴክኖሎጂን መጠቀም እና የአሠራር ሥርዓትን ለንግዱ ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ለሸማቹም በአዲስ መልኩ የሚያስለምዱ ይሆናል።

ሌላው በረዳት ፕሮፌሰር ፍሬዘር የተገለፀው፤ ባለሀብቶች መጥተው በግብይቱ ውስጥ ሲሳተፉ ዋናው እስከታችኛው ማህበረሰብ ድረስ ተጠቃሚ ማድረግ ይችላሉ። አዳዲስ ምርቶችን፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና አዳዲስ አሠራሮችን እና የግብይት ሥርዓቶችን ለነጋዴው ብቻ ሳይሆን ለሕብረተሰቡም ያስተዋውቃሉ። ይህ እንዳለ ሆኖ ሲመጡ ለሥራው ይዘው የሚመጡት ካፒታልም ለኢኮኖሚ መነቃቃት የሚኖረው ድርሻ የሚናቅ አይደለም።

በኮተቤ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር እና ተመራማሪው ሙህዲን መሐመድ በበኩላቸው፤ በሀገሪቱ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ለውጭ ባለሀብቶች መፈቀዱ ያልተለመደ አዲስ ነገር ነው። በርግጥ ጥቅም እና ጉዳቱ ተጠንቶ፤ ጉዳቱን ለመቀነስ ጥቅሙን ለመጨመር በርካታ ሥራዎች መሠራት አለበት ይላሉ።

እንደ መምህሩ ገለፃ፤ የትኛውም ነገር ጥቅም እና ጉዳት ይኖረዋል። ዋናው ጉዳይ ያንን ሚዛን ለማስተካከል የመጫወቻ ኳሶችን መጠቀም ነው። እነዛን ኳሶች ይዞ በአግባቡ መጫወት ከተቻለ የተሻለ ጥቅም ማግኘት ይቻላል። በኢትዮጵያ ትናንሽ ነገሮችን ጨምሮ ብዙ ነገሮች የሚመጡት ከውጭ ነው። ባለው የፀጥታ ችግርም ምክንያት እንቅስቃሴው የተገደበ በመሆኑ እና በሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያ በውጭ ምርት ላይ ጥገኛ ሆናለች።

ከዚህ ቀደም በጣም ጥቂት ሰዎች ምርትን ከውጭ እያመጡ ገበያውን ይቆጣጠሩ ነበር። በእነርሱ ምክንያት በተጋነነ ዋጋ ለዛውም በብዛት የማይገኝበት ሁኔታ ነበር። አሁን ግን በሰፊው ሊገኝ ስለሚችል፤ የውድድር መንፈስን ያመጣል። ይህ ሸማቹን በእጅጉ የሚጠቅም ይሆናል። ስለዚህ ንግዱ ለውጭ ባለሀብት ሲፈቀድ የውጭ ምርቶች በአነስተኛ ዋጋ በተሻለ ጥራት የሚገኙበት ዕድል የሚፈጥር መሆኑን መምህር ሙህዲን አብራርተዋል።

ሌላኛው ጥቅም የውጭ ባለሀብቶች መምጣታቸው የሚያመጣው የሥራ ዕድል አለ የሚል እምነት እንዳላቸው በመጠቆም፤ እነዚህ ሰዎች ሲመጡ ሙሉ ለሙሉ ሠራተኞቻቸውን ከውጭ ይዘው አይመጡም። ስለዚህ ኢትዮጵያውያንን መቅጠራቸው አይቀርም። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቴክኖሎጂ ሽግግር ይኖራል። አሠራራቸውንም ለማወቅ ያስችላል ብለዋል።

ለውጭ ባለሀብቶች በርን በመክፈት እንዲነግዱ መፍቀድ የነፃ ገበያ ሥርዓት መገለጫ መሆኑን አስታውሰው፤ እዚህ ላይ በአብዛኛው ሸማች ተጠቃሚ ይሆናል። አንድ ሸማች ወደ ገበያ ሲሔድ የሚያያቸው ነገሮች አሉ። አንደኛው የተሻለ ዋጋ፤ የተሻለ ጥራት እና በቀላሉ መግዛትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለመግዛት ይዘጋጃል። የውጭ ባለሀብት መግባቱ እንደሸማች እነዚህን የተሻሉ ዕድሎች ይሰጣል። ይህንን ሸማቹ ካገኘ የሻጩ ማንነት አያገባውም። ኢትዮጵያዊም ሆነ አሜሪካዊ ወይም ቻይናዊ ቢሆን ምንም ችግር የለውም። በተጨማሪም ሀገር ውስጥ ያለውን ምርት በቀላሉ ለማሰራጨት ይጠቅማል በማለት መምህር ሙህዲን ጥቅሙን አስመልክቶ አስረድተዋል።

ነገር ግን የውጭ ባለሀብቶች መሳተፍ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ጉዳትም ሊኖረው እንደሚችል የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ አመልክተዋል። አንደኛው ተወዳዳሪ መሆን ያልቻሉ እንጭጭ (አነስተኛ) የሀገር ውስጥ የንግድ ማህበረሰብ አካላት ከግብይት ሊወጡ ይችላሉ የሚል ስጋት እንዳላቸው ረዳት ፕሮፌሰር ፍሬዘር ገልጸዋል። በሌላ በኩል የውጭ ባለሀብቶች ሀገር ውስጥ ነግደው እና አትርፈው ያገኙትን ሀብት ወደ ውጭ ሀገር የማሸሽ ዝንባሌ ካላቸው እና ይህ በሕግ ሥርዓት ካልታሠረ ምናልባትም የሀገር ሀብት በቀላሉ ከሀገር እንዲሸሽ ያደርጋል ብለው እንደሚያስቡም ረዳት ፕሮፌሰር ፍሬዘር አመላክተዋል።

መምህር ሙህዲን በበኩላቸው፤ በጉዳትነት የጠቀሱት የሀገር ውስጥ ምርትን ያዳክማል የሚል ነው። በዚህ ሳቢያ የውጭ ምርት ማራገፊያ የመሆን ዕድል ሊያጋጥም ይችላል ይላሉ። በተጨማሪ ከባዱ ጉዳይ በእነዚህ አካላት ላይ የዋጋ ቁጥጥር ለማድረግ ይከብዳል የሚል ስጋትም አለባቸው። ቀደም ሲል መንግሥት በንግድ ላይ ቁጥጥር ያደርግ ነበር። እነዚህ ግን የውጭ

> **የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ እንደተናገሩት፤ የውጪ ባለሀብቶች በንግድ ሥርዓቱ ውስጥ በመሳተፋቸው ተጠቃሚው የሚሆነው መላው የኢኮኖሚ ሥርዓቱ ነው። ገዢም ሻጭም ይጠቀማሉ**

ሀገር ኩባንያዎች ናቸው። ዓለም አቀፍ ገበያውን መሠረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው መንግሥት ሊቸገር ይችላል ብለዋል።

የሀገር ውስጥ ምርት ከተዳከመ አምራቾች እንደቀድሞ ማምረት ካልቻሉ እና አነስተኛ ነጋዴዎችም ከሥራ ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ የሚፈጥረው ጫናም ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ይህንን ሚዛን ለማስጠበቅ በቅድሚያ የሀገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር አቅማቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። የማበረታቻ ዘዴዎችን መጠቀም የግድ መሆኑንም ጠቁመዋል።

« የሀገር ውስጥ አምራችም ሆነ ነጋዴ መኖሩ ሀገር በተለያየ መልኩ ተጠቃሚ ትሆናለች። » ያሉት መምህር ሙህዲን፤ ሁሉንም ነገር ለውጭ ካምፓኒ መተው ማለት ሀገርን አደጋ ላይ መጣል በመሆኑ ሚዛኑን ማስጠበቅ እንደሚገባ አስረድተዋል። የመንግሥት ሕግን የማስፈፀም አቅምም ማደግ እንዳለበት ጠቁመዋል። የውጭ ባለሀብቶች ሙሉ ለሙሉ እንዳይቆጣጠሩት እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሙሉ ለሙሉ ከገበያው ውጭ እንዳይሆኑ አስቀድሞ ሕግን የማስከበር ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባልም ብለዋል።

ትልቁ ጉዳት እና ጫናው በአምራቹ ላይ መሆኑን በማስታወስ፤ በጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ላይ በሚሳተፉ ሰዎች ላይ ጫና ይፈጥራል። የሀገር ውስጥ ነጋዴዎች ተፎካክረው የሚነግዱበትን ዕድል መፍጠር ከተቻለ ጉዳቱን መቀነስ ይቻላል ብለዋል። በሸማቾች በኩልም እነዚህ ሸማቾች ገብተው ሙሉ ለሙሉ የሀገር ውስጥ ምርትን የሚቆጣጠሩ ከሆነ በሂደት የገበያ ሥርዓቱ በትክክል ካልተመራ ሁሉንም ግብይት መቆጣጠር (ሞኖፖሊ) ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸውም ተናግረዋል። ይሄ ደግሞ በረዥም ጊዜም ቢሆን አሁን ያለው ችግር ተመልሶ የመከሰት ዕድል ሊኖረው ይችላል። ይህ ችግር እንዳይፈጠር ሕግን የማስከበር አቅማችን ወሳኝነት አለው ብለዋል።

የኢትዮጵያውያን የግብይት ሥርዓት እጅ ባህላዊ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ፍሬዘር፤ ሻጩ ብቻ ሳይሆን ሸማቹም ላይ ያለውን ክፍተት ያብራራሉ። በምሳሌ ሲያስረዱ ሳይንስም ሆነ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው በአንድ ምርት ላይ ዋጋ ሲጨመር ፍላጎት ይቀንሳል። ማለትም በምክንያትም ሆነ ያለምክንያት የዋጋ ጭማሪ ካጋጠመ ገዢ አይኖርም። በኢትዮጵያ ግን የአንድ ምርት ዋጋ ቢጨምር ሸማቹ ምንም ዓይነት ምላሽ አይሰጥም። ነጋዴው ያለምንም ተጨባጭ ምክንያት ዋጋ ሲጨምር ሸማቹ ከመግዛት አይቆጠብም። ዋጋ ቢጨምርም ሸማች ከመግዛት ወደኋላ አይልም። ነጋዴዎች ይህንን በመረዳታቸው ዋጋ ሲጨምሩ ሽያጭ አይቀንስባቸውም። ስለዚህ ከመጨመር ወደኋላ አይሉም። በዚህ ሂደት ውስጥ ትርፋቸው በጣም በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ይመጣል። ነገር ግን ሰፊው ማህበረሰብ ክፉኛ እየተጎዳ ይሄዳል። ስለዚህ ሥርዓት የተበጀለት የግብይት ሥርዓት የለም ብለዋል።

በሕግ በተቋም ደረጃ የተስተካከለ የግብይት ሥርዓት የለም። የሆነ ሰው ተነስቶ ይጨምራል። ኢኮኖሚው ነፃ ኢኮኖሚ ነው የሚል ነገር አለ። ነፃ ኢኮኖሚ ማለት ግን ማህበረሰቡን ክፉኛ ማንገላታት እና መበደል ማለት አይደለም። ንግድ ፍቃድ የሚሰጠው ለማገልገል ነው። የሚያገለግልበት ደግሞ ማዕቀፍ አለው። ከዛ ማዕቀፍ ሲወጣ የግብይት ፈቃድ መከልከል እና ከግብይት ሥርዓት ውስጥ ማስወጣትን የመሳሰሉ ርምጃዎች ይጠበቃሉ። እናም እስከ አሁን ድረስ ገበያው ልቅ መሆኑ አነስተኛ እና ጥቂት ባለሀብቶች በአንድ ሌሊት ቱግ ብለው ከፍተኛ ባለሀብት የሚሆኑት በሰፊው ሕዝብ ላይ በሚያደርጉት ብዝበዛ ነው። ከዚህ በኋላ ይህ ይቀንሳል የሚል ዕምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

‹‹የሌሎቹ ማለትም የሽያጭ እና የግዢ ሂደቱ ዘመናዊነት ይታይበታል። በእኛ ሀገር ግን በግብይት ሠንሰለት ውስጥ አላስፈላጊ ወጭዎች አሉ። በመሃል የደላላ፣ የውል ማሰር፣ የመስማማት እና የትራንስፖርት እንዲሁም ሌሎችም በጣም ብዙ ወጪዎች አሉ። ‹‹ሀ›› የሚባል ነጋዴ ቢኖር እና ተገቢውን አገልግሎት ባይሰጥ፤ ሸማቹ ‹‹ለ›› የሚባል ነጋዴ ጋር ቢሄድ የተሻለ አገልግሎት አያገኝም። ሸማቹ ሌላ ‹‹መ›› የተባለ አገልግሎት ሰጪ ጋር ቢሄድም ከሁለቱ የተለየ አገልግሎት አይሰጠውም። ሻጮች ግንኙነት (ኔትወርክ) ያላቸው ናቸው። የመረጃ ፍሰት አላቸው። ይህ ሸማቹን ሲጎዳ መኖሩን ረዳት ፕሮፌሰር አመልክተዋል።

ንግድ ተወዳዳሪነት አምስት ብርም ቢሆን ቀንሶ ሽጦ ማትረፍ ቢያስፈልግም የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ግን በተቃራኒው ዋጋቸው አንድ ዓይነት ነው። ስለዚህ ገዢ የሚገዛው ነጋዴ ባለው ነው። ሸማቹ አማራጭ የለውም። ሁሉም አንድ ነው። ነገር ግን አሁን በቀላሉ ወዲያው የውጭ ባለሀብቶች ወደ ንግድ ሲገቡ በሸማቹ ላይ አሁን እንዳለው በግንኙነት (ኔትወርክ) ተፅዕኖ ለማምጣት ጊዜ ይወስዳል። ስለዚህ ይህ ችግር እንዳይመጣ የሀገር ውስጥ ነጋዴዎች ከገበያ ከመውጣታቸው በፊት ቀድመው ዝግጅት ማድረግ አለባቸው።

በአጠቃላይ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ እንደተናገሩት፤ የውጭ ባለሀብቶች በንግድ ሥርዓቱ ውስጥ በመሳተፋቸው ተጠቃሚው የሚሆነው መላው የኢኮኖሚ ሥርዓቱ ነው። ገዢም ሻጭም ይጠቀማሉ። በገዢው በኩል አማራጭ ይገኛል። የተሻለውን መርጦ የመግዛት ዕድል ይኖረዋል። ሻጭ አዳዲስ ቴክኖሎጂ እና የግብይት ሥርዓቶችን ይማራል። ያልተለመዱ የአሠራር ሥርዓቶችን ያውቃል፤ ራሱን አሻሽሎ ተወዳዳሪ ለመሆን ይሞክራል። ተወዳዳሪነትን ማሳደግ በራሱ አንደኛው ጥቅም ነው። ጥራትንም ያሳድጋል። ሸማችም ይጠቀማል፤ ደንበኛ ንጉስ ነው የሚለው በእውን የሚታይ ይሆናል ብለዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በ‹‹ስታርት አፕ ኢትዮጵያ›› ዓውደ ርዕይ ላይ ካገኘናቸው ወጣቶች አንዷ.....

**አስመረት ብስራት**

ሀገረ ኢትዮጵያ ከዘመኑት እኩል ዘምና ከፍ ያለች ሀገር እንድትሆን የቴክኖሎጂ ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ይህንኑ በመረዳትም ካደጉት ሀገራት እኩል ለመራመድም ሀገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት ሀገር ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት እያደረገች ትገኛለች። በሁሉም መስክ ማለትም የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል፣ ዘመናዊ ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ግብርናን ዘመናዊ በማድረግ በምግብ እራስን ለመቻል፣ ለጤና ብሎም ለወታደራዊ አገልግሎት፣ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ቴክኖሎጂ መሠረታዊ ነገር ነው።

የቴክኖሎጂ አቅም ማደግም ከሀገር ውስጥ አገልግሎትን ከማሻሻል አንስቶ በውጭ ሀገራት ለሚገኙ በዚህ ዘርፍ ያሉ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችን ለማሟላት የራሱን አስተዋፅኦ የሚያደርግ ነው።

አሁን ላይ ኢትዮጵያ ለቴክኖሎጂ ልማት ሰፊ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኑን በመንግሥት ይገለፃል። የዚሁ አካል የሆነ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ያዘጋጀው ‹‹ስታርት አፕ ኢትዮጵያ›› ዓውደ ርዕይ ከመጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ሲካሄድ ሰንብቷል። ለሦስት ሳምንታት በዘለቀው ዓውደ ርዕይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በፋይናንስና በሌሎች ዘርፍ የተሰማሩ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ‹‹ስታርት አፖች›› ሥራዎቻቸውን በማስተዋወቅ ላይ ሰንብተዋል።

በእለቱ በርካታ ወጣቶች በቴክኖሎጂው ዘርፍ ሥራን ፈጥረው ለውጭ ሀገራት ካምፓኒዎች በማገልገል ዶላር የሚያመጡ ወጣቶች መኖራቸውን ሰማን። እውነት ሀገራችን በዚህ ልክ ሙያተኞች አላት ወይ በማለት ልቤን ሳስጨንቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሜሪካ ውስጥ ለሚገኘው ለማክዶናልድ ለተባለ ምግብ አቅራቢ ተቋም የሚሰሩ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች መኖራቸውን በ‹‹ስታርት አፕ ኢትዮጵያ›› ዓውደ ርዕይ ላይ ተናገሩ። ታዲያ ይህን ተስፋ ሰጪ ጅምር ከግቡ እንዲደርስ ሰዎችን የማብቃት ሥራ ከሚሰሩት መካከል አንዷን ጠጋ ብለን አነጋገርን።

ፍልቅልቅ ወጣት ናት። ቀርቦ ላላያት ይህን ያህል ቁም ነገር ውስጧ የያዘች አትመስልም። ለቃለ ምልልሱ ተስማምተን መናገር ስትጀምር ግን ከእድሜዋ በላይ የበሰለች ሆና አገኘኋት። የሃያ አራት ዓመት ወጣት ስትሆን ገሊላ ደስታ ትባላለች፡፡ የምትሰራው ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አውትሶርሲንግ ላይ ነው።

ወጣቷ ኢ-ቴክ በተባለ ድርጅት ውስጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አውትሶርሲንግ ዲፓርትመንት ኃላፊ ሆና በማገልገል ላይ ትገኛለች። ይህ ድርጅት ለባንኮችና ለተለያዩ ተቋማት በርካታ የሳይበር ደህንነት ሥራዎችን የሚሰራ ነው። የሶፍትዌር ዲቨሎፐመንት፤ ቴሌኮምና ኢንፍራስትራክቸር፤ ኢኮሜርስና ፊንቴክስ አገልግሎቶችንም እንዲሁ ለተለያዩ ተቋማት ሰጥቷል።

የተቋሙ ዋና ትኩረት የሳይበር ደህንነትና ሶፍትዌሮችን የማበልፀግ ሥራ፤ ቴሌኮምና ኢንፍራስትራክቸር ሥራን ጨምሮ የሚሠራ ሲሆን እሷ የምትመራው ዲፓርትመንት የአውትሶርሲንግ ሥራን ይሠራል። አውትሶርሲንግ ሥራው ከላይ የጠቀስናቸው በተቋሙ የሚሰሩ ሥራዎችን ወደ ውጭው ገበያ ማለትም ወደ አሜሪካ ወደ አውሮፓ ወስዶ እዛ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ማለት ነው።

ወጣቷ እንደምታብራራውም እሷ የምትመራው ዲፓርትመንት ቴክኖሎጂ ላይ ያለውን አቅም በስልጠና በመስጠት በውጭ ሀገራት ያሉ ገበያዎችን ያፈላልጋል፡ ፡ ወጣቶች ባሉበት ሀገር እንዲሳተፉ በማድረግ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ሥራዎች ወደ ሀገር ውስጥ መጥተው እንዲሠሩ የማድረግ ሥራን ያከናውናል።

ገሊላ በልጅነቷ ግሎሪ የተባለ ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ተምራለች። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በካቴድራል ተምራ ያጠናቀቀችው ወጣት በጥሩ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ወጤት አርሲ አሰላ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ዓለም አቀፍ ንግድና የመዋዕለ ነዋይ ፈሰስ አስተዳደር ትምህርት ተምራ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ተመረቀች። አሁን ሁለተኛ ዲግሪዋን በኢንተርናሽናል ትሬድ ኤንድ ኢኮኖሚክስ እየተማረች ትገኛለች።

የመጀመሪያ ዲግሪዋን እንደተመረቀች ኢንቨስትመንትን የሚያማክር አንድ ተቋም ውስጥ ዳታ አናሊስት በመሆን ነበር ሥራ የጀመረችው። በመቀጠል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አውትሶርሲንግ ዳይሬክተር በመሆን በመሥራት በተማረችው የዓለም አቀፍ ንግድ ላይ ባለሙያዎችን ለገበያ ማቅረብ ሥራንና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተለያዩ ሥራዎችን ከሚሰሩ አካላት ጋር የማገናኘት ሥራን መሥራት ቀጠለች።

ከነበረችበት የደታ አናሊስስት ሥራ ወጥታ የአውት ሶርሲንግ ሥራ ላይ ስትገባ ወደ ቴክኖሎጂ ለመቅረብ ከፍተኛ እድል እንደፈጠረላት የምትናገረው ወጣት በአንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚያልቅ ቋሚ ሠራተኛ ለማያስፈልጋቸው ካምፓኒዎች የሚፈለገውን ሥራ መሥራት የአውትሶርሲንግ ሥራ በማለት ይታወቃል ትለናለች።

አንድ ተቋም የራሱ የሆነ ሶፍትዌር ማበልፀግ ቢፈልግ ቋሚ ሠራተኛን ከሚቀጥር ይህን ሥራ ሥራዬ ብለው ለሚሰሩ ተቋማት ሰጥቶ የሚፈለገውን ሶፍትዌር አስለምቶ የሚጠቀምበት አሠራር ለበርካቶች የሥራ እድል የፈጠረ ተቋማትንም ከተጨማሪ ወጪ የሚያድን መሆኑን ተናገራለች።

አውትሶርሲንግ ሲባል ሰፊ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ሲሆን የቴክኖሎጂ አውትሶርሲንግ ላይ የምትሰራው ወጣት ገሊላ አሁን ባለችበት ተቋም በሀገር ውስጥ ያሉ በርካታ የሶፍት ዌር ኢንጅነሮች በማሰልጠን ላይ ትገኛለች፡፡ ተመርቀው ከተቀመጡት በተጨማሪ በየዓመቱ የሚመረቁና ገበያውን የሚቀላቀሉትንም በማሰልጠን ወደ ሥራ ለማስማራት ደግሞ የግድ ገበያውን የሚያገናኝ አካል በማስፈለጉ ነው የአውት ሶርሲንግ ሥራ የሚሠሩ ተቋማተ ያስፈለጉት። ሥራው ሥራ ፈላጊውንና ሥራን የማገናኘት ሲሆን የቴክኖሎጂ አቅም ያለውን ሰው በማሰልጠን ብቁ ሰው ለገበያው ማቅረብ እንደሆነ ትናገራለች።

እንደ ገሊላ ገለፃ በሥራው ውስጥ ኦን ሹርና ኦፍ ሹር የሚባል የአውት ሶርስን እስታይል አለ። ይህ ማለት ኦፍ ሹር ከአንድ ሀገር እሩቅ ማለትም ከሚሰራለት ካምፓኒ እሩቅ ሆኖ የሚሠራ ሥራ ሲሆን ኦን ሹር ደግሞ ሥራው አካባቢ ሆኖ መሠራት ማለት ነው። አሁን በአውትሶርሲንግ ሥራው የአውሮፓና የአሜሪካ|ን ገበያ ለመያዘ እየተሞከረ ነው። ይህ ሲባል አንድ የምግብ አቅራቢ ተቋም ትእዛዞችን እየተቀበለ ለሼፎቹ የሚያስተላልፍ የአይቲ ባለሙያ ቢፈለገ አሜሪካ ላይ አንድ ሰው የሚቀጥርበት ገንዘብ አንድ አስረኛው ኢትዮጵያ ውስጥ ሊያስቀጥረው ከቻለ ተቀጣሪውም በሀገሩ ሆኖ በዶላር እየተከፈለው መሥራት ሲችል ይህ ገበያን የማገናኘት ሥራ ለሥራውም ለሠራተኛውም ጥቅም አለው ማለት ነው።

በየዓመቱ የሚመረቁ የሶፍትዌር ኢንጂነሮች፤ የአይቲ ባለሙያዎችም የዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ያለን ሥራ በመሥራት በሀገራቸው ተቀምጠው ራሳቸውን ጠቅመው ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪን እንደሚያስገኙ ትናገራለች።

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አውትሶርሲንግ ዓለም አቀፋዊ ሰፊ ገበያ አለው። በብዛት በህንድ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች በደቡብ አፍሪካ ያሉ ባለሙያዎች በሥራው ይሳተፋሉ። በእነዚህ ሀገራት የሚኖሩ ባለሙያዎች ከአስር በመቶ ያላነሰ ገቢ ከአውት ሶርሲንግ እንደሚያገኙ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱ ወጣቷ ትናገራለች።

በሀገር ውስጥ ያሉ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ሀገሪቱ ያላትን ርካሽ የሰው ጉልበት በመጠቀም የሥራ አጦችን ቁጥር መቀነስ ይቻላል። በሀገራችን ያለው ታይም ዞን ማለትም ሰዓት አቆጣጠራችን ለብዙ ሀገራት የተመቸ መሆኑ፤ በቴክኖሎጂው የሰለጠኑ ወጣቶች መበርከታቸው በተወሰነ ስልጠና ለገበያው የተስማሙ ብቁ አቅም ያላቸው ወጣቶች መኖራቸው የውጭውን ፍላጎት ለመያዝ ያስችለናል ትለናለች።

በቂ ስልጠናዎች ስለሚሰጡ አዲስ የሚመጣ ቴክኖሎጂን በፍጥነት ተግባብቶና ተረድቶ መሥራት እንደሚቻል የምትናገረው ወጣት አሁን ስልጠናዎችን በቀላሉ በኢንተርኔት ማግኘት በሚቻልበት በዚህ ዘመን በቀላሉ ሰልጥነው ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም የሚችሉ ወጣቶችን ማፍራት ይቻላል ብላለች።

እንደነዚህ ዓይነት <<የስታርት አፕ ኢትዮጵያ>> ዓውደ ርዕይ መከፈቱ ብዙ የማይተዋወቁ ሥራ ፈጣሪዎች እንዲገናኙ የሚያደርግ ሲሆን በዚህም የማይቻሉ የሚመስሉ ነገሮች እርስ በእርስ ግንኙነት ተችለው እንዲታዩ ያደርጋል ብላለች።



ወጣት ገሊሳ ደስታ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቴክኖሎጂው ዓለም ውስጥ በርካታ እቅም ያላቸው፤ የቴክኖሎጂ እውቀታቸው የላቀ ሴቶች እየተፈጠሩ መሆኑን የምትናገርው ወጣት ገሊላ ሴቶች ቴክኖሎጂን የመረዳት አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑ ለዚህ አስተዋፅኦ እንዳለው ትናገራለች።

አሁን ያለው የትምህርት ሁኔታ በተለይም በከተማ አካባቢ ሴቶችን የሚያበቃ ነው። ከቴክኖሎጂ አንድ ነገርን ይዞ በትእግስት የመጨረስ አቅም የላቸውም ሴቶች ናቸው። ሴቶች ይህንን ሥራ መሥራታቸው በራሱ ሌላ አቅም የሚፈጥር ነው።

በሚገርም ሁኔታ ሴቶች አግብተውም፤ ወልደውም ቤት ውስጥ ሆነው መሥራት የሚችሉበት ሥራ የቴክኖሎጂ ሥራ ነው። በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ትምህርት ማግኘት በእጅ ያለ ስለሆነ በስልክ መማር እና በስልክ መሥራት የሚቻልበት ነገሮች የቀለሉበት ጊዜ ነው።

አንድ እናት የቴክኖሎጂ ባለሙያ ከሆነች ልጅ ወልዳ ቤት መሆን ቢኖርባት ሥራዋን የማቆም ግዴታ የለባትም። ይህም ማለት በቴክኖሎጂ ሥራ ላይ የተሳተፈች ከሆነች ልጇን እየተንከባከበች ከሥራዋ ሳትርቅ መቆየት እንደምትችል ትናገራች።

የቴክኖሎጂ ሥራ የሚሠራው በአእምሮ በመሆኑ ሴቶች እናትነትንና የቤተስብ ኃላፊነትን እየተወጡ ቴክኖሎጂ ላይ መሥራት ይቻላል። ሴትነት የሰጣቸው መልካም ፀጋዎች በጊዜያቸው ወብ ሆነው እንዲቀጥሉ ሴቶች በተሻለ ለቴክኖሎጂ ቅርብ የሆኑ ሥራዎቹን መሠራት አለባቸው የሚል እምነት እንዳላት ትናገራለች።

በዚህ ዘመን ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች የበዙበት፤ ወጣቱ መማር የሚፈለግ፤ የሚጓጓ ወጣት ያለበት ዘመን ነው። ሴቶቹም ወደፊት የመግፋት፤ አዲስ ነገር የማግኘት ጉጉታቸው የላቀ በመሆኑ የመፍጠር እና አዲስ ነገር የማግኘት ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ያንን ደግሞ ሊደግፉ የሚችሉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ በመሆኑ ሀገሪቱ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የምታገኘው ጥቅም እየላቀ የሚመጣበት ተስፋ ይታየኛል ብላለች።

በሀገሪቱ በርካታ ሶፍትዌር ኢንጂነሮች መገኘታቸው፤ ሥራ ፈጣሪዎች መበራከታቸው፤ በቀደመ ጊዜ ከነበረው በተለየ ለቴክኖሎጂ ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ መስክ ወደፊት እንደምትራመድ አመላካች ነው፡፡

ከታላላቆቹ እኩል መራመድ እንችል ዘንድ፤ እየተፈጠረ ያለውን የቴክኖሎጂ ግብዓት የታጠቀ ትውልድ ማፍራት አስፈላጊ ነው። ስለዚህም አሁን ስታርት አፖችን ለማበረታታት የተወሰደው ዓይነት ገንቢ አስተዋጽኦ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል በሚል ሃሳባችንን በዚሁ ቋጨን፡፡ ቸር ይግጠመን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አዲስ ዘመን በትውስታ ማህደሩ ውስጥ በርካታ ጉዳዮችን እያስታወሰ ዛሬም ያስገርመናል፡፡ ከዘመን ዘመን አድማሱን እያሰፋ ዛሬን በደረሰበት መንገድ፤ የሚያስታውሰን ብዙ አለ፡፡ ዛሬ ከሚያስታውሰን ርዕሰ ጉዳዮች በቁጥር ከፍ ያሉት፤ ወንጀል ነክ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህም፤ ወህኒ ቤት ገቡ ይለናል፤ ለመሆን የገቡት ማናቸው? የግብጹን ፕሬዚዳንት በአዲስ አበባ ለመግደል የወጡት ሦስቱ አሸባሪዎች የመጨረሻው እጣፈንታቸው ሞት ሆኗል፡፡ ደራሲው ማሞ ውድነህ “ዋሻ ይሠራሉ” ሲል እኛስ ለምን? በማለት ከሚመጣው የጦርነት ቅኝቱ ያካፍለናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከአንባቢው የጥያቄና የሃሳብ ድግሶች መካከል ጥቂቱን በ”አንድ ጥያቄ አለኝ” ስር ከጳውሎስ ኞኞ ምላሾች ጋር ሰፍረዋል፡፡

### ወህኒ ቤት ገቡ

በአንዲት የሞተች ጥጃ ምክንያት በተነሣው የወንጀል ክርክር አንዲት የ30 ዓመት ሴት ፤ዘጠኝ ልጆቻቸውን ጥለው ወህኒ ቤት መግባቸውን ከአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተገኘው ዜና ታውቋል፡፡

እመት እልፍነሽ ወልደየስ የተባሉት የልጆች እናት ወህኒ ቤት ለመግባት ዋና ምክንያት የሆነባቸው አንዲት ጥጃ ገዝተው አርደዋል ተብለው ተከሰው ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ ነው፡፡

በተከሳሿ ላይ የቀረበው የዓቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያመለክተው ፤ጥጃዋ ከታረደች በኋላ ተደርሶበት የቀረቡት ምስክሮች ቆዳዋ የተገኘው ጥጃ እመት ጌጤ የተባሉትን ሴት ጥጃ ትመስላለች በማለት ምስክሮች ባሰሙት ቃል ብቻ መሆኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ይገልጣል፡፡

እመት እልፍነሽ ፤በሞተች ጥጃ ምክንያት ተከሰው አዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት ቀርበው በ፫ ወር እሥራት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸው ወህኒ ቤት መግባታቸውን የተከሳሿ ጠበቃ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ ገልጠዋል፡፡

(አዲስ ዘመን የካሪት 18 ቀን 1965 ዓ.ም)

### ተቆጣጣሪ በመምሰል ያጭበረበረው ተቀጣ

ደሴ፣ ኢዜአ በደሴ ከተማ ውስጥ ምንም አይነት ሥልጣን ሳይኖረው የአሥር አለቃ ነኝ በማለት ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባውንና የሚወጣውን እህል፣ ስኳርና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች በመፈተሽ ሲያወናብድ የተገኘው ዓሊ መሐመድ በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የ04-01-01 ቀበሌ ማኅበር የፍርድ ሸንጎ ከትናንት በስቲያ ወስኖበታል።

በተከሳሹ ላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት የቻለው ባልተሰጠው ሥልጣን በመንገድ ላይ እየጠበቀ ስኳርና ሸቀጥ ጭነው ወደ ገጠር የሚወጡትንና እህል ጭነው ወደ ከተማ የሚገቡትን መኪናዎች እያስቆመ በመፈተሽ የተመቸውን ጥቅም በመቀበል ሲለቅ ያልተመቸውን ደግሞ ወደ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ በማቅረብ አወናብዶ ለማስቀጣት ሞክሮ እንደነበር በማረጋገጡ ነው፡፡

(አዲስ ዘመን የካቲት 19 ቀን 1969ዓ.ም)

### በሦስቱ አሸባሪዎች ሳይ የሞት ቅጣት ተበየነ

(ኢ.ዜ.አ) የግብጹን ፕሬዝዳንት ሆስኒ ሙባረክን አዲስ አበባ ላይ ለመግደል የሞከሩና ሁለት ኢትዮጵያውያንን ገድለው ሶስቱን ያቆሰሉ አሸባሪዎች በሞት እንዲቀጡ ትናንት ያስቻለው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወሰነ፡፡ የፍረፍድ ቤቱ ቃል አቀባይ እንዳስታወቀው ሰውፊት ሃሰን፣ አብዱል ቃኒ፣ አብዱል ከሪም አብዱልናዲና አልአረብ ሳዲቅ ሃፊዝ በተባሉ ግብጻውያን ላይ ቅጣቱ የተበየነው አቃቤ ህግ ያቀረበባቸው ማስረጃ በዝግ ችሎት ላይ ሲመለከት በነበረው ፍረፍድ ቤት በመመረጋገጡ ነው፡፡

(አዲስ ዘመን መስከረም 11 ቀን 1989ዓ/ም)

### ዋሻ ይሠራሉ

በዛሬው በዚህ በሚያሠጋው ጊዜ ድንገት አንዱን ቀን የሚፈራው የ3ኛው የዓለም ጦርነት የተነሣ እንደሆን ሽማግሌዎች፤ አሮጊቶች፤ ሕጻናቶች ከተቻለም ቁስለኞች የሚገቡበት ዋሻ በየቦታው እየተሠራ ነው፡፡ ይህንንም ዋሻ የሚሠሩት ሰዎች በትርፍ ጊዜያቸው ፈቃደኛ የሆኑት ናቸው፡፡ ዋሻው ከሚቆፈርበት ቦታ ድረስ የሚሄዱት መኪና ያላቸው በራሳቸው መኪና ሲሆን፤ የሌላቸው ደግሞ የሚሄዱት በነጋዴዎችና በልዩ ልዩ ማኅበር ሥር በሚያገለግሉት አውቶብሶች ትላልቅ መኪናዎችና በታናናሽ የቤት አውቶሞቢሎች ነው፡፡ ይህም ሥራ የሚሠራው በሌላ አገር ነው እንጂ በኛ ሀገር መስሏችሁ ውሸት ነው እንዳትሉኝ ሌላዎቹ ሀገሮች ይህን ሲሠሩ እኛስ ምነው?

ማሞ ውድነህ(ዋግ ድሃና)

አንድ ጥያቄ አለኝ

-አዘጋጅ ጳውሎስ ኞኞ

*የወንድሜ ጥርስ ሁለቱ ከወለቀ ሦስት ዓመቱ ነው፡፡ ከዛሬ ነገ ይበቅላል ስንል ምንም አላወጣም፡፡ ጥርሱ የሚወጣው በስንት ዓመቱ ነው?

እመቤት ሽፈራው

-አሁን ዕድሜው ስንት ነው? ድዳም ሆኖ እናዳይቀር ከጥርስ ሐኪም ዘንድ ወስዶ ማሳየቱ ያስፈልጋል፡፡ ያለዚያ ሊበላሽ ይችላል፡፡

*በጥንት ጊዜ ዝንጀሮ ሰው ነበር የሰው ገንዘብ ተበድሮ በልቶ የሚከፍለው ስላጣ በብረት ምጣድ ተቃጥሎ ወደ ዝንጀሮነት ተለወጠ ይላሉ፡፡ እውነት ነው ወይንስ አፈ-ታሪክ ነው?

ወ/ት ቀለመወርቅ በላይ

-ያፍ ታሪክ ነው፡፡

*ከሥራ ወጥቼ እስከ ምሽቱ 6 ሰዓት ድረስ ለማምሸት እፈልጋለሁ፡፡ ከጓደኞቼ ጋር መጫወት እፈልጋለሁ፡፡ ግን ሚስቴ ከሥራ ወጥተህ እንደ ዶሮ መስፈር አለብህ ትላለች፤ ትጨቀጭቀኛለች፡፡ ብመክር ባስመክር አልሰማ አለች፡፡ ልፍታት?

-እንደሱ አይደለም ጌታው እኔንም አይቆጡኝና ሚስትዎን በድለዋል፡፡ ከሰው ከቤትዎ ማምሸት ይልመዱ፡፡ እንደራስዎ ይዩት፡፡ ነገሩ ተገላብጦ ሚስትዎ ከውጭ እያመሹ እርስዎ ቤት እንዲጠብቁ ቢደረግ ይወዳሉ ? ተናደው የቤቱን ሳህን ሁሉ ይፈጁ ነበር፡፡ የሚያስመሽዎ ጓደኞችዎም መጥፎዎች ናቸውና ይሸሹ፡፡ ጨዋ አባወራ ይሁኑ እንጂ ሚስትዎን አይፍቱ፡፡ ለመሆኑ እንዲያው ግን ለመሆኑ አመልዎን ሳያስተካክሉ ለምን ሚስት አገቡ?

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 12 ቀን 1958ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ



## በጎርፍ ከ80 ሰዎች በላይ የሞቱባት ኬንያ የትምህርት ቤቶች መክፈቻ በሳምንት አዘገየች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጎርፍ ከ80 ሰዎች በላይ የሞቱባት ኬንያ የትምህርት ቤቶች መክፈቻ ዕለትን በሳምንት አዘገየች።

አውሎ ንፋስ በቀላቀለ ዝናብ ምክንያት በጎርፍ የተጥለቀለቀችው ኬንያ ትምህርት ቤቶችን መክፈት ለተማሪዎቹ እና ሰራተኞቹ ስጋት መሆኑን ገልጻለች።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በመላው ሀገሪቷ ያሉ ትምህርት ቤቶች በጎርፍ ምክንያት ጉዳት እንደደረሰባቸው የትምህርት ሚኒስትሩ ኤዚኪየን ማቾጉ እሁድ እለት ባወጡት መግለጫ አስፍረዋል።

“በከፍተኛ ሁኔታ እየጣለ ያለው ዝናብ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ላይ ያደረሰው ጉዳት እጅግ የከፋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጎርፍ አደጋን የመከላከል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን ህይወት አደጋ ላይ መጣል የማይታሰብ ነው” ሲሉ ሚኒስትሩ አክለዋል።

በኬንያ የሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ለሁለተኛ መንፈቅ ዓመት ሚያዝያ 21 ቀን 2016 ዓ.ም መከፈት ቢኖርባቸውም በጎርፍ ምክንያት የሚከፈቱበት ጊዜ ወደ ሚያዝያ 28 ቀን ተራዝሟል።

አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በጎርፍ ምክንያት ተፈናቅለው የሚገኙ ነዋሪዎች መጠለያ ሆነዋል።

ቅዳሜ ዕለት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች 13 አስከሬኖች መገኘታቸውን ተከትሎ በጎርፍ የሞቱ ሰዎች ቁጥር 83 አድርሶታል። በቀጣዮቹ ቀናትም የከፋ ዝናብ እንደሚጥል ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ የሟቾች ቁጥር ሊጨምር ይችላል ተብሏል።

ከሞቱት በተጨማሪ በጎርፍ አደጋ ከ130 ሺህ በላይ ነዋሪዎች መፈናቀላቸውን የሀገሪቱ ባለስልጣናት የገለጹ ሲሆን በርካቶች ደግሞ ደብዛቸው ጠፍቷል ተብሏል።

ኬንያን ጨምሮ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት መነሻው ከፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ በሆነው እና በአካባቢ በሚፈጠር የውሃ ሙቀት መጨመር በሚከሰተው ኤልኒኖ የአየር ክስተት ምክንያት በከፋ ዝናብ ተመትተዋል።

በዚህም ምክንያት ኬንያን ጨምሮ ጎረቤቶቿ ብሩንዲ እና ታንዛንያ ሰብዓዊ ቀውስ ውስጥ ገብተዋል።

በብሩንዲ ከ100 ሺህ ሰዎች በላይ ሲፈናቀሉ፣ በታንዛንያ ደግሞ ቢያንስ 150 ሰዎች ሞተዋል።

## የዩኬው የፓርላማ አባል ቻይናን በመተቸታቸው ከጂቡቲ እንደተባረሩ ተናገሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የዩናይትድ ኪንግደም ወግ አጥባቂ የፓርላማ አባል ቻይና ላይ ባቀረቡት ትችት ጂቡቲ ከመግባት እንደተባረሩ ተናገሩ።

ከቻይና ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላት ጂቡቲ ከጥቂት ሳምንት በፊት እንዳባረቻቸው ቲም ሎውተን ገልጸዋል።

የምሥራቅ ዎርቲንግ እና ሾረሃምን ግዛቶችን በመወከል የፓርላማ አባል የሆኑት ቲም ሎውተን ጂቡቲ ሲደርስ ከሰባት ሰዓታት በላይ በእስር መቆየታቸውን እና ወደ ጂቡቲ እንዳልገባ ተከልክያለሁ ብለዋል።

ከሶስት ዓመት በፊት በቻይና ማዕቀብ የተጣለባቸው ሎውተን በሁኔታው ብቸኝነት እንደተሰማቸው “በጣም አስፈሪ” እንደነበር ተናግረዋል።

የቻይና የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ክሱ መሰረተ ቢስ ነው ብሏል።

የፓርላማ አባሉ ወደ ጂቡቲ ያቀኑት ለአንድ ቀን ሀገሪቱን ለመጎብኘትና በሀገሪቱ ከተቀመጡትም የዩናይትድ ኪንግደም አምባሳደር ጋር ለመገናኘት ነበር።

ጂቡቲ ከደረሱ በኋላ እንዳይገቡ እና በሚቀጥለው በረራ ተሳፍረው እንደሄዱም አስረድተዋል።

“ይህ የቻይና ኮሚኒስት መንግሥት እጅ ምን ያህል ረዥም እንደሆነ የሚያሳይ ሌላ ምሳሌ ነው። በተለይም በአንዳንድ አፍሪካ ሀገራት ያላቸው የከፋ ተጽዕኖ አሳሳቢ ነው” ሲሉ ሎውተን ለቢቢሲ ተናግረዋል።

“ሆኖም ቻይና እያደረሰችው ያለው መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ተቃውመው ለመናገር በደፈሩ እና ይህንን ለመናገር መድረክ ባጡ ስፍር በሌላቸው ሰዎች ላይ እየደረሰ ያለው ማስፈራራት ከባድ ስጋት ይፈጥራል” ብለዋል።

ከሶስት ዓመታት በፊት ቻይና በሀገሪቱ ላይ “ሃሰተኛ እና የተሳሳተ መረጃ” እያሰራጩ ነው ባለቻቸው ቲም ሎውተንን ጨምሮ በአምስት የፓርላማ አባላት ላይ ማዕቀብ ጥላለች።

ይህም የዩናይትድ ኪንግደም በሀገሪቱ ባሉት ኡጉር አናሳ ሙስሊም ማህበረሰብ አባላት ላይ እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ አስመልክቶ ለወሰደችው እርምጃ አጸፋዊ የበቀል ምላሽ ነው ተብሏል።

የቀድሞው ሚኒስትር እና ሆም አፌይርስ የተሰኘው መስሪያ ቤት ኮሚቴ አባል ከ27 ዓመታት የፓርላማ ቆይታ በኋላ በቀጣይነት በሚካሄደው ጠቅላላ ምርጫ በእጩነት እንደማይቀርቡ አስረድተዋል።

# ስፖርት





# የፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በኦሮሚያ አጠቃላይ አሸናፊነት ተጠናቀቀ

**ዓለማየሁ ግዛው**

ሁለተኛው የኢትዮጵያ ታዳጊ ፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በሲዳማ ክልል አስተናጋጅነት ለአራት ተከታታይ ቀናት በሀዋሳ ስታዲየም ሲካሄድ ቆይቶ በኦሮሚያ ክልል አጠቃላይ አሸናፊነት ተጠናቋል። በውድድሩ ዕድሜያቸው ከ16 እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተወጣጡ ታዳጊ አትሌቶች በተለያዩ ርቀቶች የሩጫ እና የሜዳ ተግባራት ፉክክሮችን ማድረግ ችለዋል። የኦሮሚያ ክልልም በሰበሰበው የሜዳሊያ ብዛትና ነጥብ የውድድሩ አጠቃላይ አሸናፊና የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችሏል።

በየትኛውም ስፖርት ከታዳጊ የሚጀመሩ ስልጠናዎች ቀጣይነት ያለውን ውጤታማነት ማምጣት እንደሚቻል ይታመናል፡፡ የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲም ይህንኑ የሚደግፍ እንደመሆኑ እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆናቸውን ታዳጊዎች በዚህ ፕሮግራም ታቅፈው እንዲሰለጥኑ፣ የማሰልጠኛ ማዕከላትና አካዳሚዎች ግብዓት እንዲሆኑ ከዚያም ወደ ክለቦችና ብሔራዊ ቡድኖች እንዲያድጉ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ስልጠናውን ለመመዘን እንዲሁም ታዳጊዎቹ የውድድር ልምድ እንዲያገኙም ውድድሮች በተለያዩ ደረጃዎች ይዘጋጃሉ፡፡

ከእነዚህ መካከል አንዱ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሚያዘጋጀው የኢትዮጵያ ታዳጊ ፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሲሆን፤ በዚህ ስፖርት የሚሰለጥኑ ታዳጊዎችን ያወዳድራል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ በተደረገው በዚህ ውድድር ላይም በቀጣይ ኢትዮጵያን የማስጠራት አቅም ያላቸው ተስፈኛ ተተኪዎች ታይተዋል፡፡ ለአራት ተከታታይ ቀናት በተካሄደው ውድድርም የኦሮሚያ ክልል ባሳየው ብልጫ የበላይነቱን በመያዝ ዋንጫውን ወስዷል። የውድድሩ ተረኛ አዘጋጅ የሆነው የሲዳማ ክልል በሰበሰባቸው ነጥቦች ሁለተኛ ደረጃን ሲይዝ፤ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ደግሞ በወንዶች ሶስተኛ በመሆን አጠናቋል። በሴቶችም በተመሳሳይ ኦሮሚያ ክልል ከፍተኛውን ነጥብ በማስመዝገብ የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ የሲዳማ ክልል እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደግሞ ሁለተኛና ሶስተኛ ሆነዋል፡፡

በአጠቃላይ ውጤትም የኦሮሚያ ክልል በሰበሰባቸው በርካታ ሜዳሊያዎችና ነጥቦች ታግዞ የመጀመሪያውን ስፍራ ይዟል። የውድድሩ ድምቀትና ተፎካካሪ የነበረው የሲዳማ ክልል በተከታይነት ውድድሩን ሲያጠቃልል፤ ሌላኛው ጠንካራ ተወዳዳሪዎችን ይዞ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ ቡድን ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ጨርሷል።

ከእድሜ ጋር በተያያዘ የተለመደው የተገቢነት ችግር ቢስተዋልም በአንጻሩ ታዳጊና ተስፈኛ አትሌቶች በየርቀቱና በሜዳ ተግባራት አበረታች ፉክክሮችን ማድረግ ችለዋል። በውድድሩ ማጠቃለያ ዕለት ከተካሄዱ ውድድሮች መካከል ከ16 ዓመት በታች የሪሌ ውድድር ከፍተኛ ፉክክርን አስተናግዶ ሲዳማ በ3:47:88 በሆነ ሰዓት አንደኛ በመሆን የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ መሆን ችሏል። ማዕከላዊ ኢትዮጵያ 3:88:95 ሰዓት አስመዝግቦ ብር እና ኦሮሚያ 3:49:57 በሆነ ሰዓት በመግባት ሶስተኛና የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት መሆን ችሏል።

ከ18 ዓመት በታች የድብልቅ ሪሌ ውድድርም እንዲሁ ኦሮሚያ፣ ትግራይ እና አዲስ አበባ ጥሩ ፉክክር በማድረግ ኦሮሚያ 3:38:99 ሰዓት በመግባት ወርቁን ወስዷል። ከፍተኛ ተፎካካሪ የነበረው የትግራይ ክልል በ3:41:60 የብር ሜዳሊያውን ሲወስድ አዲስ አበባ 3:4567 የሆነ ሰዓት አመዝግቦ ነሃሱን ሊወስድ ችሏል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ ውድድሩ በደመቀና ባማረ መልኩ ተካሂዶ መጠናቀቁን ተናግረዋል፡፡ በተለይ በሴት አትሌቶች ምልመላና ምርጫ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአንጻራዊነት ያሳተፏቸው አብዛኛዎቹ አትሌቶች በተገቢው ዕድሜ የተገኙ መሆኑ የውድድሩ ጠንካራ ጎን ነበር። አንዳንድ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በበኩላቸው በተገቢ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ አትሌቶችን አለማሳተፋቸው የውድድሩ ክፍተት ነበር። ለዚህም እስከ መጨረሻው ክትትልና ምርመራ እንደተደረገና በቀጣይ ክፍተቱ የሚታረምበት ሁኔታ እንደሚኖርም ጠቁመዋል።

በመጀመሪያ ዙር ምርመራ 70 ዕድሜ ያጭበረበሩ አትሌቶች የተለዩ ሲሆን፤ ሌሎች ማስረጃዎች ተይዞ የምርመራ ሥራው እንደሚቀጥል አስረድተዋል። የዕድሜ ማጭበርበር ከዚህ በኋላ እንደይኖር የልየታ ሥራ የሚሰራና ቀጣይ በሚወሰነው መሠረት ሕጉን በማይተገብሩት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ርምጃ ይወሰዳል ተብሏል። ከዚህም በተጨማሪ የሚሰጠውን የዋንጫ ሽልማት በማስቀረት ለአትሌቶች ብቻ ማበረታቻ ሜዳሊያ የሚሰጥም ይሆናል። የሕክምና ባለሙያዎች ቀድመው ክልልና ከተማ አስተዳደር በመሄድ ምርመራ በማድረግ የመለየት ሥራም ሌላኛው የዕድሜ ማጭበርበርን ለመከላከል የሚጠቅም መንገድ ሊሆን እንደሚችልም አስረድተዋል፡፡



**የኦሮሚያ ክልል በቻምፒዮናው ባሳየው የበላይነት አጠቃላይ አሸናፊ በመሆን ዋንጫውን ወስዷል፣**



# በድጋሚ የወጣ የሃራጅ ጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ

ስማቸው ከዚህ በታች የተጠቀሱት ተበዳሪ ከቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ የወሰዱትን ብድር ባለመክፈላቸው ተቋሙ ከዚህ በታች የተመለከተውን በዋስትና የተያዘ የመኖሪያ ቤት ባለበት ሁኔታ በጨረታ ይሸጣል፡፡

| ተ ቁ | የተበዳሪው ስም | የዋሱ ስም | ብድር የወሰዱበት ቅርንጫፍ | የሚሸጠው ንብረት | ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻ | | | የንብረቱ ዓይነት | የካርታ ቁ እና የቦታ ስፋት | የጨረታው መነሻ ዋጋ | የጨረታ ሽያጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሪት መሰረት ክ/ ጊዮርጊስ | አቶ ክ/ጊዮርጊስ ለገሰ | ሃሩፋ ቅርንጫፍ | ቤት | ከተማ | | | ቤት | የካርታ ቁ 18137<br>-የቦታ ስፋት 105 ካ.ሜ | 1,500,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር/ | ቀን | ሰዓት |
| | | | | | ሻሸመኔ | | | | | | ግንቦት 13/2016 ዓ.ም | ከጠዋቱ 4፡00 |

**ማሳሰቢያ**

1- ማንኛውም ተጫራች ወይም ህጋዊ ወኪሉ ¼ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ክፍያ ማዘዣ /ሲፒኦ/ በማስያዝ መጫረት ይችላል፡፡

2- አሸናፊው ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ በ15 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያለበት ሲሆን ካልከፈሉ ለጨረታ መነሻ ያስያዙት ገንዘብ ተመላሽ አይደረግም፡፡

3- ቤቱ ያለበትን ሁኔታ ለማየት በቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ ጽ/ቤት በሻሸመኔ ከተማ በሃሩፋ ቅርንጫፍ አማካኝነት ከጨረታ በፊት ባሉ የስራ ቀናት እና የጨረታው ቀን በቦታው በመገኘት መመልከት ይቻላል፡፡

4- በንብረቱ ላይ ከመንግስት የሚፈለጉ ግብሮችን ቫት የስም ማዛወሪያ እና ሌች ወጪዎችን የጨረታ አሸናፊው ይሸፍናል፡፡

5-ተቋሙ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስተጨማሪ መረጃ** በስልክ ቁጥር 0910017849 መደወል ይችላሉ፡፡

## ቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ

# የጨረታ ማስታወቂያ

በደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መንግስት የካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ለወረዳ ግብርና አ/ጥ/ህ/ስ ጽ/ቤት በምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮግራም በጀት ድጋፍ በ 2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በወረዳው ሽሎ ቀበሌ ቡልካቡልክ አትክልትና ፍራፍሬ መጋዘን ግንባታ ስራ ህጋዊ ስራ ተቋራጮችን በጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

**በዚህም መሠረት**

- ለመስኖ ስራ BC/GC/ ደረጃ 7 ከዚያ በላይ ግንባታ ፈቃድና ብቃት ማረጋገጫ ያለው
- ለ2016 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ ም/ወረቀት የተ/እ/ታ/ቫት ምዝገባ ም/ወረቀት የግብር ከፋይ መለያ /TIN/ ም/ወረቀት እንዲሁም በዘርፉ በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ የሚያስችል በአቅራቢነት ስለመመዝገባቸው የም/ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ በጨረታው መሳተፍ ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 30 ቀናት ውስጥ በሥራ ሰዓት ብቻ ለዴቻ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የማይመለስ 400.00 ብር አራት መቶ ብር ብቻ በመክፈል ከመ/ቤታችን የምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮግራም ግዢ ቢሮ ቁጥር 06 መውሰድ ይችላሉ።
- ተጫራቾች ኦርጅናል ፋይናንሻል ሰነድና ቴክኒካል መረጃዎችን በአንድ ፖስታ በማሸግና ፋይናሻል ሰነዶችን ሁለት ኮፒ በፖስታ በማሸግ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠሩ ተከታታይ 31ኛ ቀን ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ በ31ኛ ቀን 10፡00 ሰዓት ታሽጎ 10:30 የሚከፈት ይሆናል። ዕለቱ ሥራ ቀን ካልሆነ በቀጣዩ የሥራ
- ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል።
- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 50,000(ሀምሳ ሺህ ብር) በባንክ በተመሰከረ የክፍያ ማስያዣ (CPO) ብቻ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
- መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታዉን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0477720383/0917101540 ደዉለዉ መረዳት - ይችላሉ፡፡

## በደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መ/ካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት